# አማርኛ

## እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## ፪(2)ኛ ክፍል


**አዘጋጆች**

ሙሉቀን ፈንታ መኮንን

አሻግሬ ግባቱ ገበየሁ

አዲስዓለም አሸኔ ለማ

**ገምጋሚ**

መስፍን ደፈረሱ ወ/መድህን

ትንቢት ግርማ ሀይሉ

ፋሲል ብዙነህ በቀለ

**የጥራት ክትትል**

ፍሬህይወት አሰፋ ከበደ

**አቀማመጥ (layout) እና ስዕል (illustration)**

እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ (TMS)

**አስማሚዎች**

ሰመረ ኃይሉ ይግለጡ

አግአዚት ገብሩ ተሻለ



ኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ትምህርት ቢሮ

# ምስጋና

ይህ መጽሐፍ በትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ ካርታ ምክረ ሐሳብ መሰረት በኢፌዲሪ ትምህርት ሚንስቴር ተዘጋጅተው የቀረቡትን የሥርዓተ ትምህርት መጽሐፍት ማዘጋጃ ሰነዶችን መነሻ በማድረግ በአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ የማስማማት ዝግጅት የተደረገበት ሲሆን የማስማማት ዝግጅቱና የሕትመት ወጪው በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስትና በኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራም-ኢ/GEQIP-E/ ተሸፍኖአል፡፡

በመሆኑም መጽሐፉን የማስማማት ዝግጅት ተደርጎበት መጠቀም እንዲቻል ለፈቀደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ፣ የማስማማት ዝግጅቱን በገንዘብ፣ በሰው ሃይልና በማቴሪያል፣ ልምዳቸውንና ዕውቀታቸውን በማጋራት ለረዱ፣እንዲሁም ሌሎችም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለደገፉ አካላት፣ተቋማትና ግለሰቦች ሁሉ የሲዳማ ትምህርት ቢሮ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

## ©የቅጂ መብት.

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት የአዲስ አበባ አስተዳደርና የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ትምህርት ቢሮዎች ናቸው፡፡

© 2014፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ድሞክራሳዊ ሪፓብልክ ትምህርት ሚኒስቴር፤ የቅጂ መብት ሙሉ የተከበረ ነው፡፡ ያለፈቃድ ማተም፣ ማባዛት፣ ባልተገባ መንገድ ማከማቸትና በሃርድ ኮፒም ሆነ በሶፍት ኮፒ ማሰረጨት እንዲሁም ላልተገባ ዓላማ መጠቀም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ድሞክራሳዊ ሪፓብልክ፤ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 410/2004 ቅጂ መብት እና ጥበቃ ደንብ መሰረት ያስቀጣል፡፡

የመጀምሪያ እትም 2016 ዓ.ም

ሲዳማ/ ሃዋሳ

# ማውጫ


ይዘት ገጽ

መግቢያ..........................................................IV

ምዕራፍ አንድ፡- ልብስ.............................................1

ምዕራፍ ሁለት፡- ወቅቶች..........................................12

ምዕራፍ ሶስት፡- ታሪኮች...........................................24

ምዕራፍ አራት፡- የአትክልት ቦታ...............................34

ምዕራፍ አምስት፡- የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ...............46

ምዕራፍ ስድስት፡- ባህላዊ ሙዚቃ...............................59

ምዕራፍ ሰባት፡- መልካምሥነምግባር..........................70

ምዕራፍ ስምንት፡- የምግብ አዘገጃጀት.........................80

ምዕራፍ ዘጠኝ፡- ዲጅታል ቁስ....................................89

ምዕራፍ አስር፡- የዱር እንስሳት..................................98

ዋቢ መፅሐፍት

# • መግቢያ

## ለተጠቃሚዎች

ይህ መፅሐፍ የ፪ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን በመጀመሪያ ቋንቋነት ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡በዚህ መፅሃፍ የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መፃፍ እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀ የመጀመሪያ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት አካል ነው፡፡

መፅሐፉ ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው ተማሪዎች ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ እንዴት እንደሚማሩ ማለማመድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ይህ መፅሃፍ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት እና መርሃ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆዎችን አካቷል፡፡

## መርህ አንድ

ተማሪዎች ስዕሎችን በመመልከት ተረቶችን(ታሪኮች) የማዳመጥና የመናገር ክሂላቸውን ያዳብራሉ፡፡

## መርህ ሁለት

ተማሪዎች የሚነበብላቸውን ታሪክ(ምንባብ) በሚገባ በማዳመጥ ያዳመጡትን ታሪክ(ምንባብ) በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በግልፅ ቋንቋ መናገርና መፃፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህንን ተግባር ለማድረግ ተከታታይ የመናገርና የመፃፍ ተደጋጋሚ ልምምድ ማድረግ አለባቸው፡፡

## መርህ ሶስት

ተማሪዎች የቋንቋው ተተኳሪ ፊደላት የሚወክሏቸውን ውስብስብና ሞክሼ ፊደላትን ተገቢ የሆነ የፊደላት አሰዳደር ሥርዓት በመጠቀም አዳዲስ ቃላትን ይማራሉ፡፡

## መርህ አራት

ተማሪዎች በውስብስብና ሞክሼ ፊደላት የተመሰረቱ ቃላትንና ዓረፍተ ነገሮችን ማንበብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## መርህ አምስት

ተማሪዎች ተዘውታሪ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የተዘውታሪ ቃላቱን ፍቺ አብረው መማር አለባቸው፤ በዚህም የሚያዳምጡትንና የሚያነቡትን ይረዳሉ፤ የቃላት ዕውቀታቸውንም በማሳደግ ሐሳባቸውን በንግግርና በፅሑፍ በአግባቡ ይገልፃሉ፡፡

## መርህ ስድስት

ተማሪዎች የተለያዩ ታሪኮችን(ተረቶችን) እና ሌሎች ፅሑፎችን አንብበው መረዳት ይችሉ ዘንድ የአንብቦ መረዳት ተግባራትን በተደጋጋሚ በመስራት ማዳበር ይተበቅባቸዋል፡፡

# • ምክር ለወላጆች

ውድ የተማሪ ወላጆች(አሳዳጊዎች)

ልጆቻችን የቋንቋውን ትምህርት በአግባቡ ይገነዘቡ ዘንድ የእኛና የእርስዎ ጥምር እገዛ ያስፈልጋል፤ ስለሆነም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ከግምት ውስጥ በማስገባት በቤት ውስጥ ልጅዎን ያግዙ፡፡

፩. ለልጅዎ የተለያዩ ታሪኮች፣ ተረቶች ወዘተ ይንገሯቸው ወይም ያንብቡላቸው፡፡

፪. ለልጅዎ የነገሯቸውን ታሪክ(ተረት) መልሰው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

፫. በተማሪ መፅሃፍ ላይ የቀረቡትን ምንባቦችና ተግባራት በየጊዜው እየተከታተሉ ያሰሯቸው፡፡

፬. ልጆችዎ በራሳቸው ተነሳሽነት እንዲያዳምጡ፣እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡና እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡

፭. ልጆችዎ መምህሮቻቸው የሚሰጧቸውን ተግባራዊ ክንውን መተግበሪያ ሚሆኑ ቁሳቁሶች እና ሌሎችን በማሟላት የወላጅነት ግዴታዎን ይወጡ፡፡

አማርኛ

፩ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አንድ

## ልብስ

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የምታዳምጡትን ምንባብ አጠቃላይ ሐሳብ ትለያላችሁ፡፡
- ከተሰጣችሁ ፅሑፍ ውስጥ ዋናውን ሐሳብ ትናገራላችሁ፡፡
- ለተለመዱ ቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ባለ ሶስት ሆሄ ቃላትን ታጣምራላችሁ፤ ትነጥላላችሁ፡፡
- ሆሄያትን አቀናጅታችሁ ቃላት ትጽፋላችሁ፡፡

## ማዳመጥ

### ልብስና መስሪያዎቹ





### ቅድመ ማዳመጥ

1. ተማሪዎች እናንተ ምን አይነት ልብስ ለብሳችኋል?
2. ከላይ ያሉትን ስዕሎች በማየት ስለምን እንደምታዳምጡ ገምቱ?

### አዳምጦ መናገር

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

1. ልብስ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ቡሉኮ ከምን ይሰራል?

### ቃላት

፩. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የጎደሉትን ፊደላት በምሳሌው መሰረት በጽሑፍ አሟሉ፡፡

ምሳሌ፡- ል__ስ = ልብስ

1. ___ራብ
2. ቀሚ___
3. ___ጠላ
4. ጃ______ት

፪. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉ ፊደላትን በማቀያየር ሌሎች ቃላትን መስርቱ፡፡

| ምሳሌ፡- ለበሰ = በሰለ፣ሰለበ |
|---|

1. ቀለበ = ________
2. ቀጠነ = ________
3. ማለዳ = ________
4. በደለ = ________
5. ልብስ =________

☞ ## ሞክሼ ፊደላት

**ሞክሼ ፊደላት** የምንላቸው በፊደል ገበታ ላይ የተለያየ ቅርጽ ያላቸው፣ በድምጽ ግን ተመሳሳይ የሆኑ ፊደላት ናቸው፡፡

በፊደል ገበታ ላይ ያሉ ሞክሼ ፊደላት

| | | |
|---|---|---|
| ሀ | ሐ | ኀ |
| ሠ | ሰ | |
| አ | ዐ | |
| ጸ | ፀ | |

፩. በምሳሌው መሰረት የሞክሼ ፊደላትን ዝርያዎች ፃፉና አንብቡ፡፡

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምሳሌ | ሠ<br>ሰ | ሡ<br>ሱ | ሢ<br>ሲ | ሣ<br>ሳ | ሤ<br>ሴ | ሥ<br>ስ | ሦ<br>ሶ | አ<br>ዐ | ኡ<br>ዑ | ኢ<br>ዒ | ኣ<br>ዓ | ኤ<br>ዔ | እ<br>ዕ | ኦ<br>ዖ |
| | ሀ | | | | | | | ጸ | | | | | | |
| 2. | ሐ | | | | | | | ፀ | | | | | | |
| 3. | ኀ | | | | | | | | | | | | | |

፩. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ሞክሼ ፊደላት የያዙትን ቃላት ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- አየለ ዐይኑ ስለታመመ ሀኪም ቤት ሄደ፡፡

- አየለ • ዐይኑ • ስለታመመ • ሀኪም

1. ሰይድና ህልውና አስፋልት ሲሻገሩ በዜብራ ላይ ነው፡፡
2. ፀዳለ ወላጆቿን ታከብራለች፡፡
3. ማኅበረሰቡ ባለው ኃይል ቢተባበር ሀገር ይለማል፡፡

## ንባብ





## ቅድመ ንባብ ጥያቄ

1. ስዕሉን በመመልከት ስለምን እንደምታነቡ ገምቱ?
2. ምን ምን የልብስ አይነቶችን ታውቃላችሁ?

### የበዓል ልብስ

ዕለቱ የጨንበላላ ዋዜማ ነው፡፡ በአካባቢው ልዩ ልዩ አልባሳትን የለበሱ ሰዎች ይታያሉ፡፡ዳኢቴ የተለያዩ ቀለማት ባላቸው አዝራሮችና ጨሌዎች ያጌጠና ከፌትል የተሰራ ቆሎ ለብሳለች አባቷ ደግሞ ከጥጥ የተሰራ ጎንፋ ለብሰዋል፡፡ልጃቸው ዳኢቴን በመያዝ በዓሉን ለማክበር ወጡ፡፡ዳኢቴ ድንገት የትምህርት ቤት ጓደኛዋን አየችው፡፡ ጓደኛዋ መሐመድ ጀለቢያ ለብሶ በውጭ በር ላይ ቆሟል፡፡ ቆቡን እየነካካ የበዓሉን ድባብ ይመለከታል፡፡ ዳኢቴ መሐመድን ከአባቷ ጋር አስተዋወቀችው፡፡

## አንብቦ መረዳት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆኑትን "እውነት" ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. እነዳኢቴ የሚሄዱት የጨንበላላ በዓልን ለማክበር ነው፡፡
2. የዳኢቴ ጓደኛ ሴት ናት፡፡
3. በጨንበላላ በዓል የተለያዩ ባህላዊ አልባሳት ይለበሳሉ፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

ተማሪዎች ከላይ የቀረበውን ምንባብ በግል ደጋግማችሁ ድምጻችሁን ሳታሰሙ አንብቡ፡፡ ከዚያም ድምጻችሁን በማሰማት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

### ቃላት

፩. በ “ሀ” ስር ላሉት ቃላት ከ “ለ” ስር ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ዕለት | ሀ. አየ |
| 2. ዋዜማ | ለ. ያጌጠ |
| 3. ያሸበረቀ | ሐ. ከዋናው በዓል አስቀድሞ የሚገኝ ቀን |
| 4. ተመለከተ | መ. ባልንጀራ |
| 5. ጓደኛ | ሠ. ቀን |

፪. የሚከተሉትን ምስሎች በሚገባ በመመልከት የምስሎችን መጠሪያና ያላቸውን ቀለም በምሳሌው መሰረት ጻፉ፡፡

| መገለጫ |  ምሳሌ |  |  |  |  |  |
|---|---|---|---|---|---|---|
| መጠሪያ | ሹራብ | | | | | |
| ቀለም | ቀይ | | | | | |

☞ ውስብስብ ፊደላት

ውስብስብ ፊደላት ማለት ሁለት ድምጾችን በአንድ ላይ አጣምረው የያዙ ፊደላት ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡- “ሉ” + “ዋ” = ሏ

| ውስብስብ ፊደላት በቅደም ተከተላቸው | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሏ | ሟ | ሧ | ሯ | ሷ |
| ሿ | ቧ | ቷ | ቿ | ኗ |
| ኟ | ዃ | ዟ | ዧ | ዷ |
| ጇ | ጧ | ጯ | ጿ | ፏ |

፩. ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ውስብስብ ፊደላትን ድምጻችሁን ከፍ በማድረግ ተራ በተራ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

፪. ተማሪዎች በቡድን በመሆን በምሳሌው መሰረት ከውስብስብ ፊደላት ውስጥ አራቱን መርጣችሁ ቃላት በመመስረት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- ሯ = ሯጭ፣ ጸጉሯ፣

1.____ = ____________ 3.______=_____________

2.______= ___________ 4.______= ____________

☞ ማጣመርና መነጠል

፩. የሚከተሉትን ውስብስብ ፊደላት ነጣጥላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- ሟ = ሙ-ዋ

1. ሿ = __________ 4. ጯ = __________

2. ዧ = __________ 5. ፏ = __________

3. ፗ = __________

፪. የሚከተሉትን ፊደላት በማጣመር ውስብስብ ፊደላትን መስርቱ።

ምሳሌ፡- ሱ + ዋ = ሷ

1. ጡ + ዋ =__________ 4. ቡ + ዋ =__________

2. ሩ + ዋ =__________ 5. ዡ + ዋ =__________

3. ዱ + ዋ =__________

✍ መፃፍ

፩. መምህራችሁ የሚያሳዩዋችሁን ድርጊታዊ ገለጻ በሚገባ በመመልከት ድርጊቱን በቃላት ጻፉ።

ለምሳሌ፡-



መብላት

፪. መምህራችሁ የሚነግሯችሁን ቃላት በሚገባ አዳምጣችሁ በትክክል ጻፉ፡፡

:: ?

ሥርዓተ ነጥብ ማለት ስሜትንና አገላለፆችን በጽሑፍ ውስጥ አጉልቶ የሚሳይ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል አራት ነጥብና ጥያቄ ምልክት ይጠቀሳሉ፡፡

ሀ. አራት ነጥብ (፡፡) ይህ ስርዓተ ነጥብ ዓረፍተ ነገር መጠናቀቁን ያሳያል፡፡

ምሳሌ፡- ራህመትና ዳንኤል ጎበዝ ተማሪዎች ናቸው፡፡

ለ. ጥያቄ ምልክት (?) ይህ ስርዓተ ነጥብ ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገርን ለመመስረት ይጠቅማል፡፡

ምሳሌ፡- እድሜሽ ስንት ነው?

፫. የሚከተሉትን ትግበራዎች መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ጽሑፍ ላይ ተመስርታችሁ በተግባር አከናውኑ፡፡

ሀ. መምህራችሁ በሰሌዳው ላይ የሚጽፉላችሁን ፅሑፍ በጥንድ ሆናችሁ በጥሞና ደጋግማችሁ አንብቡ።

ለ. አራት ነጥብና ጥያቄ ምልክት የሌለበትን ጽሑፍ ስታነቡ በንበታችሁ ላይ ምን ለውጥ እንዳስከተለ ተወያዩበት።

፬. በዓርፍተ ነገር ውስጥ አራት ነጥብ በመጠቀም የህይወት ታሪካችሁን ፃፉ።

ምሳሌ፡- ስሜ ደራሮ ይባላል።

የተወለድኩት ሐዋሳ ነው።

## የማጠቃለያ ተግባራት

፩. የሚከተሉትን ውስብስብ ፊደላት በሚገባ በማንበብ የተለያዩ ቃላትን መስርቱ።

| ፊደላት | የተመሰረቱ ቃላት |
|---|---|
| ምሳሌ፡-ሏ | ጣሏት፣ በሏት... |
| 1. ኋ | |
| 2. ጏ | |
| 3. ኗ | |
| 4. ሯ | |
| 5. ሷ | |
| 6. ቋ | |

፪. የሚከተሉትን ምስሎች በመመልከት ስማቸውን ፃፉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
|  |  |  |  |
| 1 | 2 | 3 | 4 |

፫. በሚከተለው ምሳሌ መሰረት የራሳችሁን የህይወት ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

## ራስን መግለፅ



- ስሜ፡- ሐያት ኢብራሒም እባላለሁ።
- አባቴ፡- ኢብራሂም መሀመድ ይባላል።
- እናቴ፡- ሰዓዳ ሁሴን ትባላለች።
- ዕድሜዬ፡- ስምንት ነው።
- ክፍሌ፡- ሁለተኛ “ለ” ነው።
- ትምህርት ቤቴ፡- ፋራ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ይባላል።
- የምኖረው፡- በታቦር ክፍለ ከተማ፣ ጢልቴ ቀበሌ ነው።
- ለወደፊት፡- መምህር መሆን እፈልጋለሁ።
- የምወደው፡- መጽሐፍ ማንበብና ሽርሽር መሄድ ነው።

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሁለት

## ወቅቶች


### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ያዳመጣችሁትን ፅሁፍ ዋና ዋና ሐሳብ በማስታወሻ ትይዛላችሁ።
- የምንባቡን ዋና ሀሳብ በቃላችሁ ትናገራላችሁ።
- ከ "ወቅቶች" ጋር ለተገናኙ ቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ።
- ድምፆችን ታጣምራላችሁ፤ ትነጥላችሁ።
- ባለ አራት ፊደል ቃላትን ትፅፋላችሁ።
- አራት ነጥብን በፅሁፍ ውስጥ ታስገባላችሁ።

## ማዳመጥ

### ኢትዮጵያና ወቅቶቿ



### ቅድመ ማዳመጥ

1. ተማሪዎች የምታስታውሷቸውን የኢትዮጵያ ወቅቶች ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. ስዕሉን አይታችሁ የምታዳምጡት ምንባብ ስለ ምን እንደሚያነሳ ገምቱ፡፡

### አዳምጦ መረዳት

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ምላሽ ስጡ፡፡

1.ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡
2.አሁን በሃገራችን ኢትዮጵያ ያለንበት ወቅት ማን ይባላል?

፬. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ ከሆነ “እውነት” ስህተት የሆነውን ደግሞ “ሐስት” በማለት መልሱ፡፡

1. የኢትዮጵያ ወራት አስር ናቸው፡፡
2. የህዳር ወር በመኸር ወቅት ውስጥ ይካተታል፡፡
3. ዝናብ የሚበዛበት ወቅት በልግ ይባላል፡፡

## ቃላት


፩. በ"ሀ" ስር ያሉትን ወቅቶች በ"ለ" ስር ካሉት ወራት ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | መልስ | "ለ" |
| --- | --- | --- |
| 1. መኸር | | ሀ. ታህሳስ |
| 2. በጋ | | ለ. ጥቅምት |
| 3. በልግ | | ሐ. ሐምሌ |
| 4. ክረምት | | መ. ግንቦት |


፪. ከአመቱ ወራት መካከል ባለ አራት ድምፅ የሆኑትን በቻርቱ ላይ አሟሉ፡፡



፫. በምሳሌው መሰረት የጎደሉትን የሳምንቱ ቀናት ሞልታችሁ አንብቡ፡፡




## 📖 ንባብ




### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. የመስከረም ወር ሲመጣ ምን ምን በዓላት ትዝ ይሏችኋል?
2. ስዕሉን በመመልከት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልፅ ገምቱ፡፡

## አበባ አየሁሽ

ሜዳና ተራራው በለምለም ሳርና አበባ አጊጧል፡፡ የጠዋቷ ፀሐይ ፍንትው ብላ ቀኑን አድምቃዋለች፡፡ የእነማሳንቱ ሰፈር ልጆች በጋራ ተሰብስበው ፀጉራቸውን ተሰርተው ሐበሻ ቀሚሳቸውን

ለብሰው ለመጨፈር ተዘጋጅተዋል፡፡ ሔለን ከበሮ ይዛለች፡፡ ማሳቱና ቡጡ ደግሞ አደይ አበባና ሳር ይዘዋል፡፡ ልጆቹም ወደ አቶ ወታሮ ቤት በር ጠጋ ብለው በጭብጨባ የአበባ አየሁሽ ጭፈራን ጀመሩ፡፡ ቡጡ ፈጠን ብላ "አበባ አየሁሽ" ስትል ሁሉም በጋራ "ለምለም" በማለት ተቀበሏት፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ቡጡ… | ባልንጀሮቼ | ልጆቹ…"ለምለም" |
| | ግቡ በተራ | ለምለም |
| | እንጨት ሰብሬ | ለምለም |
| | ቤት እስክሰራ | ለምለም |
| | እንኳን ቤትና | ለምለም |
| | የለኝም አጥር | ለምለም |
| | እደጅ አድራለሁ | ለምለም |
| | ኮከብ ስቆጥር | ለምለም |
| | ኮከብ ቆጥሬ | ለምለም |
| | ስገባ እቤቴ | ለምለም |

| | |
|---|---|
| ትቆጣኛለች | ለምለም |
| የእኔዋ እሜቴ | ለምለም |

አደይ የብር ሙዳይ ኮለል በይ (2 ጊዜ) እንዳለች አቶ ወታሮ ከባለቤታቸው ወ/ሮ ዳኢቴ ጋር በጋራ ወጥተው ለልጆቹ ብር በመስጠት መረቋቸው። እነሱም:-

ከብረው ይቆዩ ከብረው፣
በአመት አንድ ልጅ ወልደው፣
ሰላሳ ጥጃ አስረው፣
ከብረው ይቆዩ ከብረው።

ብለው በጋራ መርቀው ወደ ቀጣዩ ቤት አመሩ።

## አንብቦ መረዳት

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በፅሑፍ መልሱ።

1. አበባ አየሁሽ የሚጨፈረው በየትኛው ወር ነው?
2. አበባ አየሁሽ የሚጨፍሩት እነማን ናቸው?
3. የምንባቡን ዋና ሐሳብ በቃል ተናገሩ።

፪. በምንባቡ ውስጥ ያለው የበዓል መዝሙር በክፍላችሁ ከሚገኙ ጓደኞቻችሁ ጋር በጋራ በመለማመድ መምህራችሁ በሚያዟችሁ መንገድ በተግባር አሳዩ፡

## ☞ መነጠልና ማጣመር

፩. የሚከተሉት ቃላት በሚገባ በማንበብ በቃላቱ ውስጥ ያሉትን ሆሄያት ነጣጥላችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፡- ጳጉሜ = ጳ-ጉ-ሜ

ሀ. ሰኔ፡-____________ መ. ሐምሌ፡-____________

ለ. ጥር፡-____________ ሠ. ነሐሴ፡-____________

ሐ. ህዳር፡-____________

፪. የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት አጣምራችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ጫማ + ዎች = ጫማዎች

| ቃላት | | የተጣመሩ ቃላት |
|---|---|---|
| 1. በሬ | | |
| 2. ሱሪ | | |
| 3. አበባ | ዎች | |
| 4. ኮፍያ | | |
| 5. ሜዳ | | |

፫. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በማጣመር የተለያዩ ቃላትን መስርቱ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰ | ጠ | ቀ | 1. ቀጠረ | 6. |
| ት | ረ | መ | 2. | 7. |
| ለ | በ | ደ | 3. | 8. |
| ተ | ሸ | ከ | 4. | 9. |
| አ | ዘ | ጀ | 5. | 10. |

## 🗝 ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን የመጀመሪያ ድምፃች በሌላ ድምፃች ተክታችሁ ፃፉ። ከዚያም የሁለቱን ቃላት ልዩነት በቃል ግለፁ።

ምሳሌ፡- ሰኔ = የኔ፣ ቅኔ ...

1. ጥር =__________
2. ቀን =__________
3. ሰኞ =__________
4. በጋ = __________
5. በላ =__________

## አቀላጥፎ ማንበብ

የሚከተለውን ምንባብ በመደጋገም ትክክለኛውን የአነባበብ ሥርዓት ተከትላችሁ አንብቡ።



## አካባቢያችንን እንጠብቅ

የምንኖርበትና የምንማርበት አካባቢ ሁልጊዜም ንፁህ መሆን አለበት። አካባቢያችን ንፁህ ከሆነ በሽታ አይዘንም። ለዓይናችንም የሚያስደስት ይሆናል። ለዓይናችን ደስ የሚል ከሆነ ደግሞ ደስተኞች እንሆናለን። ይህ እንዲሆን ደግሞ እያንዳንዳችን አካባቢያችንን ማፅዳት፤ ልዩ ልዩ እፅዋትንና አበባዎችን መትከል አለብን። ይህን ስናደርግ የመሬታችን አፈርም አይሸረሸርም። ስለዚህ አንድ ተክል ስንቆርጥ በምትኩ ሌላ ችግኝ መትከል ይኖርብናል። ይህንን ካደረግን ሁልጊዜ ጤናማና ደስተኛ እንሆናለን። አካባቢያችንም ውብ ይሆናል።

(አላምረው 2002፣ 91 ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የቀረበ)

### ✍ መፃፍ

፩. ተማሪዎች መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት በሚገባ በማዳመጥ:-

ሀ. ቃላቱን በደብተራችሁ ፅፋችሁ አንብቧቸው።

ለ. የፃፋችኋቸውን ቃላት የመጀመሪያውን ፊደል አጥፍታችሁ ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

ሐ. ባጠፋችኋቸው ፊደላት ምትክ ሌላ አንድ ፊደል በመተካት በምሳሌው መሰረት ቃሉን ሌላ ፍቺ እንዲኖረው አድርጉ።

ምሳሌ:- ህዳር - ("ህ" ፊደል ስትወገድ) ዳር - ("አ" ፊደል ስትጨመር) አዳር

ህዳር፣ ዳር፣ አዳር

1. __________ ፣ __________ ፣ __________
2. __________ ፣ __________ ፣ __________
3. __________ ፣ __________ ፣ __________
4. __________ ፣ __________ ፣ __________
5. __________ ፣ __________ ፣ __________

፩. የሚከተሉትን ቃላት በዓ.ነገር ውስጥ በማስገባት የተለያየ ፍቺ እንዲሰጡ አድርጉ፡፡

ምሳሌ፡- በላ ሀ. ሰኢድ ምሳውን በላ፡፡
ለ. ሌዳሞ የውድድሩን ዋንጫ በላ፡፡

1. ሔደ
2. ዓይኖች
3. ውኃ
4. ጠላ
5. ተሾመ

፫. በሚከተለው ፅሑፍ ውስጥ አራት ነጥብ (፡፡) በማካተት ፅሑፉን የተሟላ አድርጉ፡፡

## በጋ እና ክረምት

በጋ የፀሐይ ወቅት ነው ብዙ ጊዜ ዝናብ አይጥልም ወንዞች በጣም ይቀንሳሉ እህሎች ወደ ጎተራ ይከተታሉ በጋ ለጉዞ በጣም አመቺ ነው ለከብቶች መጠጥና የግጦሽ ሳር እጥረት ይኖራል፡፡

ክረምት የዝናብ ወቅት ነው በዚህ ወቅት ብዙ ተክሎች ይበቅላሉ ወንዞች ብዙ ውኃ ይኖራቸዋል እንስሳት ውኃ እንደልባቸው ያገኛሉ ብዙ እህሎች ይበቅላሉ ገበሬዎችም በቂ ዝናብ ካገኙ ጥሩ ምርት ያገኛሉ

## የማጠቃለያ ተግባራት

፩. ከዚህ በታች የቀረበውን ፅሑፍ በትኩረት አንብቡ፤ ከዚያም ለጥያቄዎቹ ተገቢ መልስ ስጡ፡፡

### እስኪ እወቁኝ

በኢትዮጵያ ብቻ የምገኝ ብርቅዬ ወር ነኝ፡፡ አምስት ወይም ስድስት ቀናት አሉኝ፡፡ በአራት ዓመት አንዴ ስድስት ቀን እሆናለሁ፡፡ በሌሎች ዓመታት ግን አምስት ቀን ነኝ፡፡ ከነሐሴ ወደ መስከረም ድልድይ ሆኜ አሻግራለሁ፡፡ የአዲስ ዓመት ብስራት አበስራለሁ፡፡

1. እኔ ማን ነኝ?
2. የዓመቱ ስንተኛ ወር ነኝ?
3. እኔ ከየትኛው ወር በኋላ እገኛለሁ?
4. ለምንድን ነው ብርቅዬ የተባልኩት?
5. በየትኛው ወቅት እገኛለሁ?

፪. የሚከተሉትን ፊደላት በማገጣጠም ቃላት መስርቱ፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ | ጓ | እ | በ | አ | ተ | ና |
| ደ | ን | ኛ | ጫ | ች | ወ | ት |

1. ተናደደ
2. ______
3. ______
4. ______
5. ______
6. ______

፫. በ"ሀ" ስር ያሉትን ቃላት በ"ለ" ስር ካሉት ተመሳሳያቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መግራት | ሀ. እህል መክተቻ |
| 2. ንጹህ | ለ. እንደሁኔታው |
| 3. ጎተራ | ሐ. ያማረ |
| 4. እንደአስፈላጊነቱ | መ. ጽዱ |
| 5. ውብ | ሠ. ማስተካከል |

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሶስት

## ታሪኮች


### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ያዳመጣችሁትን ምንባብ አጠቃላይ ሐሳብ ለይታችሁ ቃላዊ ዘገባ ታቀርባላችሁ፡፡
- ካነበባችሁት ፅሁፍ ውስጥ አጠቃላይ ሐሳብ ትፅፋላችሁ፡፡
- በዓረፍተ ነገር ውስጥ አራት ነጥብን ትጠቀማላችሁ፡፡
- ባለአራት ፊደል ቃላትን ትመሰርታላችሁ፡፡
- ቃል አጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን በጽሑፍ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡

## አውራ ዶሮ እና ቀበሮ

### ማዳመጥ



### ቅድመ ማዳመጥ

1. ከላይ ያለውን ስዕል በመመልከት የምታዳምጡት ምንባብ ስለ ምን እንደሚያነሳ ገምቱ፡፡
2. ተረት ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

### አዳምጦ መናገር

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

ሀ. በታሪኩ ውስጥ የተራበው ማን ነው?

ለ. አውራ ዶሮው በቀበሮ የተያዘው እንዴት ነው?

ሐ. እናንተ በዶሮው ቦታ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

፪. ያዳመጣችሁትን ምንባብ በማስታወስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

፫· የምታውቁትን አንድ ታሪክ ወይም ተረት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ስርዓቱን ጠብቃችሁ በቃል ተርኩ።

🗝 ቃላት

፩. በምንባቡ መሰረት በ"ሀ" ስር ላሉት ቃላት ከ"ለ" ስር ተመሳሳይ ፍቻቸውን በመፈለግ አዛምዱ።

| "ሀ" | መልስ | "ለ" |
|---|---|---|
| 5. ተጣደፈ | | ሀ. ዘዴ |
| 6. ፈረጠጠ | | ለ. ደን |
| 7. ጫካ | | ሐ. ሮጠ |
| 8. ድርጊት | | መ. ተግባር |
| 9. ብልሃት | | ሠ. ቸኮለ |

☞ መነጠልና ማጣመር

፩. የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት በማጣመር ፃፉ።

| ምሳሌ፡- ከ - መንደር = ከመንደር<br>ዶሮ - ው = ዶሮው | |
|---|---|
| 1. ጀመረ - ች | |
| 2. አፉ - ን | |
| 3. ቀበሮ - ው | |
| 4. ወደ - ጫካ | |
| 5. ለ - መናገር | |

፪. በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በብዙ ቁጥር የቀረቡትን ቃላት ወደ ነጠላ ቁጥር በመቀየር ፃፉ።

ምሳሌ፡- ተማሪዎች = ተማሪ ደብተሮች = ደብተር

1. ቅርሶች = __________
2. መፅሃፎች = __________
3. ገበሬዎች = __________
4. በሬዎች = __________
5. ጫማዎች = __________

## ንባብ




### ቅድመ ንባብ

1. የሲዳማ ክልል ዋና ከተማ ማን ናት
2. መስህቦችን ጎብኝታችሁ ታውቃላችሁ መልሳችሁ "አዎ" ከሆነ ምን ምን መስህቦችን ጎብኝታችኋል።

# ሀዋሳ

ሀዋሳ ከተማ የተመሰረተችው በ 1952 ዓ.ም ሲሆን ከአዲስ አበባ በ 275 ኪ.ሜ ርቀት በሻሸመኔና በይርጋለም ከተሞች መካከል የምትገኝ ከተማ ናት፡፡ ከተማዋ ስያሜዋን ያገኘችው ሀዋሳ ሀይቅ ከሚለው የሲዳምኛ ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም ሰፊ የውሃ አካል ማለት ነው ፡፡ ይህች ከተማ ሰፊ ተፈጥራዊና ሰው ሰራሽ የሆኑ የታሪክ ፤ የእምነት የባህልና ዘመናዊ የሆኑ የቱሪስት መስህቦችን የያዘች ከተማ ነች፡፡

ተማሪዎች ሀዋሳ ምን ምን መስህቦች አሏት ብላችሁ ታስባላችሁ?

---

በውስጧ ከሚገኙ መስህቦች መካከል የሀዋሳ ሀይቅ፤የአላሙራና የታቦር ተራራዎች፤ ጉዱማሌና አሞራ-ገደል ፤የዓሳ ገበያ፤ የቡርቂቶ ፍል-ውሃ እና የተለያዩ ሪዞርቶች ይገኙባታል፡፡ የሲዳማ ሱሙዳና የወልደአማኑኤል ዱባለ ሀውልት፤ የሎቄ የራስ መንገሻ ቤተ-መንግስት ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ቅርሶችና መስህቦች ናቸው፡፡ ሀዋሳ የተለያየ ቋንቋና ባህል ያላቸው ማህበረሰቦች በአንድ ላይ ተሰባስበው የሚኖሩባትና በፈጣን እድገት ላይ የምትገኝ ከተማ ናት፡፡

## አንብቦ መረዳት

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. የሀዋሳ ከተማ መቼ ተመሰረተች?
2. በሀዋሳ የሚገኙ ቅርሶችና የመዝናኛ ቦታዎች እነማን ናችው?
3. ሀዋሳ ከተማ ስያሜዋን ከየት አገኘች?
4. በምንባቡ ውስጥ ስንት አራት ነጥቦች ይገኛሉ?

፪. "ሀዋሳ" ከሚለው ምንባብ ውስጥ የተረዳችሁትን ሀሳብ በሶስት መስመር በጽሑፍ አቅርቡ፡፡

### ቃላት

ከምንባብ ለወጡ ቃላት በክቡ ውስጥ ከሚገኙ ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡


1. በርካታ = ______
2. ፍቅር = ______
3. ሰላም = ______
4. ከተማ = ______
5. ድሮ = ______

ገጠር
ጥላቻ ልዩነት
ጦርነት ጥቂት
ዘንድሮ

## አቀላጥፎ ማንበብ

### እናስተዋውቃችሁ!

ቀኝ አዝማች ተስፋ ገብረስላሴ ቢልልኝ ይባላሉ። አርበኛና መምህር ናቸው። አባታቸው መምህር ገብረስላሴ ቢልልኝ ይባላሉ። እናታቸው ደግሞ ስዕለሚካኤል ወልደአብ ናቸው። የተወለዱት ታህሳስ 24 ቀን 1894 ዓመተ ምህረት በቡልጋ ክፍለ ሀገር ነው። ከእጽዋት ቀለም ያዘጋጃሉ። ብራና ፍቀው በመቃ ብዕር ይጽፋሉ። ግንቦት 26 ቀን 1992 ዓመተ ምህረት በ97 ዓመታቸው አርፈዋል። ነገር ግን ሥራቸው ትውልድ እስካለ ድረስ ይቀጥላል።



እኚህ አባት አሁን እናንተ ከቅድመ መጀመሪያ (ኬጂ) እስከ አሁን እየተማራችሁበት ያለውን "የፊደል ገበታ" የጻፉ አባት ናቸው፡፡ የፊደል ገበታን በሶስት ረድፍ በመክፈል (በሀ..ሁ..ሂ፤ መልዕክተ ዮሀንስ፤ አ..ቡ..ጊ..) በእጃቸው በመጻፍና በማሳተም ለኢትዮጵያ ህጻናት በሙሉ እንዲዳረስ አድርገዋል፡፡ ስለዚህ ሁልጊዜ ልናስታውሳቸውና ልናመሰግናቸው ይገባል፡፡ ልጆች እናንተም እንደተስፋ ገብረስላሴ ለወገንና ለሀገር የሚተርፍ ሥራ በመስራት ጎበዝ ተማሪ መሆን አለባችሁ፡፡

## ✍ መፃፍ

፩. ከላይ "እናስተዋውቃችሁ" በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ባለ አራት ፊደል ቃላትን ለይታችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ህጻናት

፪. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉትን ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- አርፈዋል = ሞተዋል

ሀ. ብዕር = ______ መ. ወገን = ______

ለ. ፊደል = ______ ሠ. ጎበዝ = ______

ሐ. ህጻናት = ______

፫. በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በማጣመር ቃላት መስርቱ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ስ | ተ | ራ | ት |
| ታ | ር | ክ | ፋ |
| ቅ | ረ | ቤ | ሪ |

ምሳሌ፡- ታሪክ

፬. በትዕዛዝ ሶስት ላይ በመሰረታችኋቸው ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱ።

ምሳሌ፡- ሀ. ታሪክ = 1. ዓባይ የዘመኑ ታሪክ ነው።

2. ብርቅነሽ የህይወት ታሪክ ጻፈች።

፭.ከተለያዩ ሰዎች የሰማችኋቸው ተረቶች ወይም ከመፅሃፍት ካነበባችኋቸው ታሪኮች መካከል አንዱን በመምረጥ ስርዓቱን ጠብቃችሁ በአጭሩ ፃፉ።

፮. አራት ነጥብን (።) እና ጥያቄ ምልክትን (?) በመጠቀም አራት ዓረፍተ ነገሮችን ሥሩ።

## የማጠቃለያ ተግባራት

1. የሚከተሉትን ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ፊደላት በማጣመር ባለ 2፣ ባለ 3፣ እና ባለ 4 ፊደል ቃላትን መስርቱ፡፡

| የተዘበራረቁ ፊደላት | ባለ 2 ፊደል ቃላት | ባለ 3 ፊደል ቃላት | ባለ 4 ፊደል ቃላት |
|---|---|---|---|
| ደ፣ ተ፣ ጠ፣ ር<br>ቸ፣ ፈ፣ ብ፣ ስ<br>ጣ፣ ረ፣ አ፣ ሰ፣ ን፣<br>ራ፣ በ፣ ጌ፣ ወ | ንብ | ሰበረ | አበጠረ |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

2. የሚከተሉትን ስርዓተ ነጥቦች በቡድን ሆናችሁ ስማቸውን እና አገልግሎታቸውን በጽሑፍ አስፍሩ፡፡ ስርዓተ ነጥቦች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

| ተ.ቁ | ስርዓተ ነጥቦች | መጠሪያ | አገልግሎት |
|---|---|---|---|
| 1. | ፡፡ | | |
| 2. | ? | | |

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አራት

## የአትክልት ቦታ

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኂላ፡-

- ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሀሳብ ትለያላችሁ፡፡
- ካነበባችሁት ፅሁፍ ውስጥ አጠቃላይ ሐሳብ ትፅፋላችሁ፡፡
- ቃል አጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን በጽሑፍ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡

## ማዳመጥ

### የወርቄ ማስታወሻ



### ቅድመ ማዳመጥ

1. በምትኖሩበት አካባቢ መናፈሻዎች (የአትክልት ቦታዎች) አሉ? መልሳችሁ አዎ ከሆነ ምን ምን የአትክልት ቦታዎች አሉ?
2. ርዕሱን እና ስዕሉን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለምን እንደሆነ ግምታችሁን ተናገሩ፡፡
3. የአትክልት ስፍራ መኖሩ ምን ጥቅም አለው?

## አዳምጦ መናገር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት  በቃል መልሱ፡፡

ሀ. ወርቂ ለምን ተሸለመች ?

ለ. ወርቂ ከአባቷ ጋር ለመዝናናት የሄደችበት ስፍራ ምን ይባላል? የትስ ይገኛል?

ሐ. እነወርቂ የጎበኙትን መናፈሻ ከሚላት ለማየት የጓጓችዉ ለምንድን ነው?

## 🗝 ቃላት

በ"ሀ" ስር ያሉትን ስዕሎች በ"ለ" ስር ካሉት መግለጫዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ስዕሎች | መልስ | መግለጫ |
|---|---|---|
| 1.  | | ሀ.ዘር መዝራት |
| 2.  | | ለ.በጋራ መስራት |
| 3.  | | ሐ.መቆፈር |
| 4.  | | መ.አበባ መትከል |
| 5.  | | ሠ.ውሃ ማጠጣት |

## መነጠልና ማጣመር

፩. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት፡-

ሀ. በሚገባ በማዳመጥ ቃላቱን በደብተራችሁ ፃፉና አንብቡ፡፡

ለ. የፃፋችኋቸውን ቃላት ቦታ በመቀያየር ሌሎች ቃላት መስርቱ፡፡

ሐ. ቦታ በመቀያየር የፃፋችኋቸውን ቃላት ላይ ሌላ ፊደል በመጨመር ቃላቱ የተለየ ፍቺ እንዲሰጥ አድርጉ፡፡

፪. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉ ሆሄያትን በመነጣጠልና በማጣመር አንብቡ፡፡

| የተነጣጠሉ ቃላት | የተጣመሩ ቃላት |
|---|---|
| 1. የ - ህፃናት | የህፃናት |
| 2. አንድ - ነት | አንድነት |
| 3. የሚ - ከበር - በት | የሚከበርበት |
| 4. እንዲ - ያስቡ - ት | እንዲያስቡት |
| 5. ሲ - መለስ | ሲመለስ |
| 6. የ - አካባቢ - ው | የአካባቢው |

ፎ. በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በነጠላ ቁጥር የቀረቡትን ቃላት ወደ ብዙ ቁጥር በመቀየር ፃፉ።

ምሳሌ፡- ሰራተኞች = ሰራተኛ

ካልሲዎች = ካልሲ

1. ቤቶች = ____________
2. ቢራቢሮዎች = ____________
3. እርሳሶች = ____________
4. ቦርሳዎች = ____________
5. መኪናዎች = ____________
6. መቆፈሪያዎች____________

## ንባብ





ቅድመ ንባብ

1. አንድን ግቢ ሊያስውቡ ከሚችሉ ነገሮች ውስጥ ጥቂቶቹን ተናገሩ?
2. ከስዕሉ የተረዳችሁትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ?

## "አበባማው ግቢ"

የህፃናት ቀን ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ በየአመቱ ሰኔ 9 ቀን ይከበራል።ይህ እንዲሆን ያደረገው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ነው። የሚከበርበትም ምክንያት የህፃናትን ደህንነት፣ ጥበቃና መልካም አስተዳደግ እንዲኖራቸው ማስቻል ነው። ይህን በማሰብ መምህርት ደግነሽ እና መምህር ጀማል ከሰኔ 5 እስከ 9 ድረስ አበቦችና የተለያዩ ችግኞች በመትከል፤ ልዩ ልዩ ፅሁፎችን በማቅረብ እንዲከበር ያደርጋሉ።

ተማሪዎች የህፃናት ቀን የሚከበርበትም ምክንያት ምንድን ነው?

ከመምህርት ደግነሽ ተማሪዎች አንዱ ሌዳሞ ነው። ሌዳሞም በህፃናት ቀን አከባበር ላይ የተከላቸውን አበቦች ሲያይ በጣም ተደሰተ። በክረምት ወቅትም አበቦችንና የተለያዩ ተክሎችን መትከልና መንከባከብ እንዳለበት አሰበ። ሀሳቡንም በተግባር ላይ አዋለው። እናቱና አባቱም በሚሰራው ስራ ደስተኛ በመሆናቸው ያግዙታል። በግቢው በርካታ አበባዎች በመተከላቸውም የእነሌዳሞ ግቢ "አበባማው ግቢ" በሚል ስም መጠራት ጀመረ። ሰዎችም የእነ ሌዳሞን ግቢ ለማየት ሁሌ ይጓጓሉ። የሌዳሞ እናትና አባትም የሰፈሩ ሰዎችን አድናቆትና ልዩ ስሜት በማየታቸው ተደሰቱ። ከአካባቢ ነዋሪዎችም ጋር መመካከር፣ በጋራ አካባቢያቸውን ማፅዳትና አበባ መትከል ጀመሩ። አካባቢያቸውም እጅግ የሚያምር፣ ፅዱና ማራኪ ሆነ።

## አንብቦ መረዳት

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሑፍ መልሱ።**

1. ተማሪ ሌዳሞ ግቢውን በአትክልት እንዲያስውብ ያነሳሳው ምክንያት ምንድን ነው?
2. እናንተ የምትኖሩበትን ግቢና አካባቢ ለማስዋብ ምን ምን መንገዶችን ትጠቀማላችሁ?
3. የህፃናት ቀን በስንት ዓመተ ምህረት መከበር ጀመረ?

**፪. "አበባማው ግቢ" ከሚለው ምንባብ ምን እንደተማራችሁ በሶስት ዓረፍተ ነገር ጻፉ።**


## 🗝 ቃላት

**፩. በሚከተሉት ፊደላት የሚመሰረቱ ቃላትን ከሳጥኑ ውስጥ በመምረጥ ከፊደላቱ ጎን ፃፉ።**


1. ተ = ተክል፣ ተማሪዎች
2. መ = ____________
3. ሐ = ____________
4. አ = ____________
5. ዐ = ____________

አፍሪካ ዐለት መናፈሻ
ሐብሎች
ዐውቀት መነፀር
መናፈሻ ተክል
ተማሪዎች ሐውልት

፱. የሚከተሉትን ምስሎች በትኩረት በመመልከት ስማቸውን በክፍት ቦታው ላይ ፃፉ።

|  |  |  |  |  |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 2. | 3. | 4. | 5. |

፲. የሚከተሉትን ፊደላት በመገጣጠም ባለአምስት ፊደል ቃላት መስርቱ።




1. ____________
2. ____________
3. ____________
4. ____________
5. ____________

## አቀላጥፎ ማንበብ

፩. ከላይ “አበባማው ግቢ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተራ በተራ እየተነሳችሁ አንብቡላቸው።

፬. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ስርዓተ- ነጥቦችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አንብቡ፡፡

1. በአሁን ሰዓት የኮሮና ስርጭት ምን ያህል ነው?
2. ችግኝ መትከል የአካባቢን አየር ንብረት ያስተካክላል ፡፡
3. ሁለተኛ ይህን መጥፎ ድርጊት ስትሰራ እንዳላይህ!
4. ሀገሬ ለእኔ ሁሉ ነገሬ ናት፡፡
5. የአባይ ግድብ በመገንባቱ እንኳን ደስ አላችሁ!
6. የስንተኛ ክፍል ተማሪዎች ናችሁ?

## ✍ ፅህፈት

፩. በምሳሌው መሰረት በሚከተሉትን ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ሳር = ልጁ ሳር ተከለ፡፡

1. አካፋ
2. አበባ
3. መኮትኮቻ
4. ውሃ
5. አፈር

### ቃለ አጋኖ (!)

ቃለ አጋኖ የመገረምን፣ የመከፋትን፣ የመደሰትን … ስሜት የምንገልጽበት ሥርዓተ ነጥብ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ልብሱ እንዴት ያምራል!

አቤት ውሸት!

፩. ቃለ አጋኖ ስርዓተ ነጥብን በመጠቀም ሁለት ዓረፍተ ነገሮችን በደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡

፫. የሚከተለውን ጽሁፍ በቡድን ሆናችሁ በሚገባ ካነበባችሁ በኋላ ከምንባቡ ሥር ያሉ ተግባራት ስሩ፡፡

## የማሳንቱ አጎት

የማሳንቱ አጎት ኡታላ ሀሜሶ ይባላል፡፡ ኡታላ ሀሜሶ የማሳንቱ አባት ወንድም ነው፡፡ እድሜው 35 ሲሆን ስራው አትክልተኛ ነው፡፡ ሙያውን የሚያከብርና ጠንክሮ የሚሰራ ታታሪ ሰራተኛ ነው፡፡ በዚህ ስራው በሐዋሳ የእፅዋት ማዕከል ውስጥ ያሉትን እፀዋት በአግባቡ በመንከባከቡ ሽልማት ተሰጥቶታል፡፡ ለወደፊት የራሱ የእፅዋት ማዕከል ከፍቶ መስራት ይፈልጋል፡፡

ሀ. ጽሁፉ እንዴት እንደተፃፈ አስተውሉ፡፡

ለ. ከቤተሰቦቻችሁ ወይም ከምታውቋቸው ሰዎች አንዳቸውን በመምረጥ ባነበባችሁት ጽሁፍ መሰረት የህይወት ታሪካቸውን በየግል ፃፉ፡፡

ሐ. በየግል የፃፋችሁትን የህይወት ታሪክ ለቡድን አባላቶቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

መ. ከፃፋችኋቸው የህይወት ታሪኮች አንዱን በመምረጥ በጋራ አዳብራችሁ ፃፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

፬. "የማሳንቱ አጎት" የሚለውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- አጎት= የአባት ወንድም


ሀ. ታታሪ = ____________ መ. ለወደፊት = ____________

ለ. ማዕከል = ____________ ሠ. ሙያውን = ____________

ሐ. ጠንክሮ = ____________

## የማጠቃለያ ተግባር

፩. የሚከተሉትን ቃላት በማጣመር ፃፉ።




| ቃላት | የተጣመሩ ቃላት |
|---|---|
| ምክር | ምክር ቤት |
| ትምህርት | |
| ፍርድ | |
| ሻይ | |
| ጎጆ | |
| መስሪያ | |

፪. የሚከተሉትን ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ፊደላት በማጣመር ባለ 3፣ ባለ 4 እና ባለ 5 ፊደል ቃላትን መስርቱ።

| የተዘበራረቁ ቃላት | ባለ 3 ፊደል ቃላት | ባለ 4 ፊደል ቃላት | ባለ 5 ፊደል ቃላት |
|---|---|---|---|
| ኢ፣ቤ፣ብ፣ን፣ጎ | | | |
| በ፣የ፣ር፣ጠ፣ | | | |
| ኸ፣ት፣ረ፣አ፣ተ | | | |
| ሪ፣ም፣ወ፣ክ፣ያ | | | |
| ል፣ማ፣ጽ፣ህ፣ስ | | | |

፫. የሚከተሉትን ምስሎች በትኩረት በመመልከት ስማቸውን በክፍት ቦታዎች ላይ ፃፉ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |  |
| 1. | 2. | 3. | 4. | 5. |

# ምዕራፍ አምስት
## የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ


### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ካዳመጣችሁት ምንባብ ለወጡ ቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ።
- ከምንባቡ ውስጥ ልዩ የሆነውን ሀሳብ ታወጣላችሁ።
- ቃለ አጋኖንና የጥያቄ ምልክትን ትለያላችሁ።
- በነጠላ ዓረፍተ ነገሮች መጨረሻ ላይ አራት ነጥብ ታስገባላችሁ።

## ማዳመጥ

### የጤና ቁልፍ




### ቅድመ-ማዳመጥ

1. ወደትምህርት ቤት ከመምጣታችሁ በፊት ምን ምን ተግባራት ታከናውናላችሁ?
2. ስዕሉን በመመልከት ስለምን እንደምታዳምጡ ገምቱ?

### አዳምጦ መናገር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን "እውነት" ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ።

1. ፀጉር ማበጠር ከአካባቢ ንፅህና ¨ይመደባል፡፡
2. ልጆቹ ተረት ለማዳመጥ የሄዱት ሰዓት አክብረው ነው፡፡
3. የግል ንፅህናን ብቻ መጠበቅ ለጤና ጠቃሚ ነው፡፡
4. መጥረግ፣ መትከልና መንከባከብ የአካባቢን ንፅህና ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ተግባራት ናቸው፡፡

## ቃላት

፩. በ "ሀ" ስር ላሉትን ቃላት ከ "ለ" ስር ተመሳሳያቸውን ፈልጉ፡፡

| ምሳሌ | "ሀ" | መልስ | "ለ" |
|---|---|---|---|
| | ተጣደፈ | ረ | ሀ. የራስ |
| 1. | ተወ | | ለ. በህብረት |
| 2. | አየ | | ሐ. ይጠቅማል |
| 3. | የግል | | መ. ሁልጊዜ |
| 4. | ዘወትር | | ሠ. ተመለከተ |
| 5. | ያስፈልጋል | | ረ. ተቻኮለ |
| 6. | በጋራ | | ሰ. አቆመ |

፪. የሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉ ፊደላትን ቦታ በማቀያየር ሌሎች ቃላት መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- በግላችን = በግ፣ በላ

1. ጥርሳችን = ______ 4. ማበጠር = ______
2. ያስፈልጋል = ______ 5. ማስጠበቅ = ______
3. መምጣት = ______

## ማጣመርና መነጠል

፩. የሚከተሉትን ተነጣጥለው የተቀመጡትን ቃላት አጣምራችሁ አንብቡና ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- የ - አካባቢ - ያችን - ን = የአካባቢያችንን

1. ወደ - ቤታ - ቸው = ______
2. እናንተ - ም = ______
3. በ - ህይወት = ______
4. ሊያ - ወሩ - ት = ______
5. ፀጉራ - ችሁ - ን = ______

፪. በምሳሌው መሰረት የሚከተሉት ቃላት መነሻ ላይ "አል-" በመጨረሻ ላይ "-ም" በመጨመር ቃላቱን አጣምራችሁ ፃፉና አንብቡ፡፡

ምሳሌ፡- ሰራ = አል- ሰራ -ም = አልሰራም

1. ታጠበ = አል- ______ -ም = ______
2. ፋቀች = አል- ______ -ም = ______
3. ፀዳ = አል- ______ -ም = ______
4. ቆረጠ = አል- ______ -ም = ______
5. ሰራች = አል- ______ -ም = ______

## ንባብ



## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች የአካባቢን ንፅህና አለመጠበቅ ጉዳት ያስከትላል? አዎ ካላችሁ ጉዳቶቹን ዘርዝሩ፡፡
2. የግልና አካባቢ ንፅህናን አንድነትና ልዩነት ተናገሩ፡፡

## "ታሞ ከመማቀቅ..."

በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖሩ ነጋዴዎች ነበሩ፡፡ ነጋዴዎቹ የተለያዩ አትክልት፣ ፍራፍሬና ጥራጥሬ እንዲሁም አልባሳትን በመሸጥ ይተዳደራሉ፡፡ ሁሉም ቤተሰቦቻቸውን የሚያስተዳድሩት ከንግድ በሚያገኙት ገቢ ነው፡፡ የአካባቢው ሰዎችም የተለያዩ ነገሮችን ከእነርሱ እየገዙ ይመገባሉ፤ ይለብሳሉ፡፡ ነጋዴዎቹ በንግድ ቦታቸው የተለያዩ ማስታወቂያዎችን ለጥፈዋል፡፡ "ዱቤ ነገ እንጂ ዛሬ የለም!"፤ "የአፍና የአፍንጫ ጭንብል ካላደረጉ አናስተናግድም!"፤ "ካለ ስራ መቆም ክልክል ነው!"...፡፡ ይሁንና ለንፅህና ብዙ ትኩረት ስለማይሰጡ የተለያዩ ቆሻሻዎችን በየቦታው ይጥላሉ፡፡

---

ተማሪዎች! ነጋዴዎቹ ለአካባቢ ንፅህና ትኩረት ባለ መስጠታቸው ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?

---

በቆሻሻው መብዛት ምክንያት አካባቢው በመጥፎ ጠረን ታወከ፡፡ ነዋሪዎቹም የቆሻሻው ሽታ ስለረበሻቸው ራቅ ወዳለ ቦታ እየሔዱ መገበያየት ጀመሩ፡፡ ሩቅ ቦታ ሔደው መገበያየታቸው ለተለያዩ እንግልት ዳረጋቸው፡፡ በዚህም በጣም መማረር ጀመሩ፡፡ነጋዴዎቹም ሰርቶ ማግኘትን ብቻ በማሰብ ደፋ ቀና ሲሉ ተራ በተራ ታመው ተኙ፡፡ ቤተሰቦቻቸውም እነርሱን በማስታመም ስለተወጠሩ የዕለት

ጉርሻቸውን ማግኘት አቃታቸው፡፡ ነጋዴዎቹም ሆኑ ነዋሪዎቹ በጣም ስለተቸገሩ በጋራ ሆነው መወያየት ጀመሩ፡፡ በውይይታቸውም አንድ የመፍትሔ ሐሳብ ላይ ደረሱ፡፡ “ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ” ነው፤ በማለት በጋራ ሆነው አካባቢያቸውን ለማፅዳትና ለመንከባከብ ተስማሙ፡፡ በቀጣዩ ቀን በጠዋት ተነስተው አካባቢያቸውን አፀዱ፡፡ ከዚያ ቀን ጀምሮ ሁሉም በደስታና በጤና መኖር ጀመሩ፡፡

## አንብቦ መረዳት

፩. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ አክብቡ፡፡

1. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሰው ሐሳብ ትኩረቱ _____ ላይ ነው?
   ሀ. የግል ንፅህና   ለ. የአካባቢ ንፅህና   ሐ. የቤት ንፅህና
2. በአንድ አካባቢ የሚኖሩት እነማን ናቸው?
   ሀ. ነዋሪዎቹ   ለ. ነጋዴዎቹ   ሐ. ሁለቱም
3. ነዋሪዎቹ ወደሌላ ቦታ ሔደው የተገበያዩት ለምንድን ነው?
   ሀ. እርስ በርስ በመጣላታቸው
   ለ. የአፍ ጭንብል (ማስክ) ባለማረጋቸው
   ሐ. አካባቢያቸው ስለቆሸሸና ስለሸተታቸው
4. ነዋሪዎቹ እና ነጋዴዎቹ ተወያይተው ምን ወሰኑ?
   ሀ. አካባቢቸውን ለቆ መሔድ
   ለ. በጋራ አካባቢን ማፅዳት
   ሐ. አለመገበያየት

፪. ምንባቡ የሚያስተላልፈውን ዋና መልዕክት በቡድን ሆናችሁ በመወያየት በሁለት ዓረፍተ ነገር ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

፩.ተማሪዎች "ታሞ ከመማቀቅ..." የሚለውን ምንባብ ተራ በተራ እየተነሳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

፪.የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክለኛ የአነባብ ስልት አንብቧቸው፡፡

ሀ. መንገድ ከማቋረጤ በፊት ግራና ቀኝ እመለከታለሁ፡፡

ለ. ቅዳሜና እሁድ ምን ትሰራላችሁ?

ሐ. እንኳን አደረሳችሁ!

## ቃላት

፩. በ "ሀ" ስር ላሉት ቃላት ከ "ለ" ስር ካሉት ቃላት ተቃራኒ ፈልጉላቸው፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
| --- | --- |
| 1. ቅርብ | ሀ. ከፊት |
| 2. ከኋላ | ለ. ይበልጣል |
| 3. መጣ | ሐ. ወደደ |
| 4. ያንሳል | መ. ሔደ |
| 5. ጠላ | ሠ. ሩቅ |

፪. በ “ሀ” ስር ባሉት ቃላት የተመሰረቱትን ዓረፍተ ነገሮች ከ “ለ” ስር በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| ሀ | | ለ |
|---|---|---|
| 1. ጤና | _____ | ሀ. የአካባቢው ውበት ይማርካል፡፡ |
| 2. ንፅህና | _____ | ለ. ቆሻሻ ለጤና ጠንቅ ነው፡፡ |
| 3. ውበት | _____ | ሐ. አካባቢን ለማፅዳት ህብረት ያስፈልጋል፡፡ |
| 4. ቆሻሻ | _____ | መ. ለሰው ልጅ ጤና አስፈላጊ ነው፡፡ |
| 5. ህብረት | _____ | ሠ. የአካባቢያችን ንፅህና እንጠብቅ፡፡ |


፫. የሚከተሉትን ስዕሎች ከመግለጫዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡



ማጠብ



መቦረሽ




ማበጠር



መጥረግ



መታጠብ



መቁረጥ

፬. የሚከተሉትን ፊደላት በመምረጥ በክፍት ቦታው ላይ በመሙላት ቃላቱን የተሟሉ አድርጓቸው፡፡

| ታ | ስ | ጉ | ፀ | ት | ሽ | ጠ | ጥ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|

1. ብሩ____
2. ፀ____ር
3. ጥር____
4. መ___ጠብ
5. ፊ_____
6. ማበ___ሪያ
7. መ____ረግ

## ☞ማጣመርና መነጠል

በምሳሌው መሰረት በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉ ሆህያትን በመነጣጠል አንብቡና በማጣመር ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡ የ - አፍሪካ = የአፍሪካ

ጊዜ - ያቸ - ው = ጊዜያቸው

1. ሸለመ - ች - ኝ = ____________________
2. አረንጓዴ - ው = ____________________
3. እየ- ተባለ = ____________________
4. የተ - መሰረተ - ው = ____________________
5. እንደ - ሚያምር = ____________________

## ✍ ጽሕፈት

፩. በክቡ ውስጥ ያሉ ቃላትን በተስማሚው ክፍት ቦታ አስገብታችሁ ዓረፍተ ነገሩን የተሟላ አድርጉ።

ንፅህና ተማሪዎች ቀን
ግል ፀጉሩን

1. ______________ ክፍላቸውን አፀዱ።
2. ሸምሱ ________________ አበጠረ።
3. ተማሪዎች የፅዳት __________ ሊኖራቸው ይገባል።
4. የግልና የአካባቢ ___________ መጠበቅ ያስፈልጋል።
5. ገላን መታጠብ የ___________ ንፅህና ነው።

፪. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት በማዳመጥ በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

፫. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ላይ አራት ነጥብ (።) በመጨመር ዓረፍተ ነገሮችን አሟሉ።

1. ጤናማ ህፃናት በአዕምሮና በአካል ብቁ ናቸው
2. ጥርስን ዘወትር መቦረሽ ያስፈልጋል
3. የግል ንፅህናችንን ከጠበቅን ጤነኛ እንሆናለን
4. ንፁህ አካባቢ ለመዝናኛ ጥሩ ነው
5. የግል ንፅህናችንን በመጠበቅ ራሳችንን ከኮሮና ቫይረስ እንከላከል

## የማጠቃለያ ተግባር

፩. የሚከተሉትን ምስሎች በትኩረት በመመልከት ስማቸውን በክፍት ቦታዎች ላይ ፃፉ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
|  1. |  2. |  3. |  4. |  5. |
| | | | | |

፪. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላት በተስማሚ ክፍት ቦታዎች ውስጥ አሟሉ።

| ሐይቆች | ላም | ሩጫ | ሱሪ | ሹካ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

1. ፓስታ በ _______ ይበላል።
2. _______ ወተት ትሰጣለች።
3. ዳንኤል _______ ተገዛለት።
4. ነገ የ _______ ውድድር አለ።
5. ኢትዮጵያ ብዙ _______ አሏት።

፫. የሚከተሉትን ቃላት መሰረት በማድረግ የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ሔደ፡-ዱካሞ ምሳውን በልቶ ሔደ፡፡

ሊጥ፡- ባልዲው ውስጥ ሊጥ አለ፡፡

1. አፈር፡- ______________________________፡፡
2. ፈረስ፡- ______________________________፡፡
3. አረሰ፡- ______________________________፡፡
4. አጠናች፡- ______________________________፡፡
5. ድልድይ፡- ______________________________፡፡

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ስድስት

## ባህላዊ ሙዚቃ

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ፅሑፍ አዳምጣችሁ ተዘውታሪ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ።
- ከሚነበበው ጽሑፍ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን በመለየት ፍቺ ትሰጣላችሁ።
- የጥያቄ ምልክትንና ቃልአጋኖን ትጠቀማላችሁ።
- ቃላትን ከመነሻ ቅጥያቸው ጋር አጣምራችሁ ትጠራላችሁ።

## ማዳመጥ

### ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች



### ቅድመ-ማዳመጥ

1. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ታውቃላችሁ? መልሳችሁ "አዎ" ከሆነ ምን ምን ታውቃላችሁ? ዘርዝሩ፡፡
2. ከስዕሉ ምን ትገምታላችሁ

## አዳምጦ መናገር

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን "እውነት" ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ፡፡



1. ከበሮ የትንፋሽ ባህላዊ መሳሪያ ነው፡፡
2. ዋሽንት አምስት ክሮች አሉት፡፡
3. ከጅማት ክርና ከእንጨት የሚሰራው ክራር ነው፡፡

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚገባ በማንበብ በቡድን ሆናችሁ በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. ከምታውቁት ባህላዊ ጭፈራ (ውዝዋዜ) የአንዱን የአተገባበር ሂደት በማስታወሻ በመያዝ በቃል ተናገሩ፡፡
2. መምህራችሁ በሚያዟችሁ መሰረት ቡድን መስርታችሁ ስላዳመጣችሁት ምንባብና ስለተወያያችሁበት ባህላዊ ጭፈራ (ውዝዋዜ) ጠቅለል ያለ ሀሳብ ጻፉ፡፡

## ቃላት

**፩. የሚከተሉትን የባህላዊ መሳሪያ መጠሪያዎች ከስዕላቸው ጋር አዛምዱ፡፡**

| ምስሎች | መልስ | መጠሪያ |
|---|---|---|
| 1.  | | ሀ. ከበሮ |
| 2.  | | ለ. ዋሽንት |
| 3.  | | ሐ. መለከት |
| 4.  | | መ. ማሲንቆ |
| 5.  | | ሠ. ክራር |

፪.የሚከተለውን የልጆች መዝሙር በሚገባ በማንበብ በተመሳሳይ ፊደል የሚጨርሱ ቃላትን ለይታችሁ አውጡ::

ጨረቃ ድንቡል ዶቃ
አጤ ቤት ገባች አውቃ
አጤ ቤት ያሉት ልጆች
እንክርዳድ ፈታጊዎች
ፈተጉ ፈታተጉ
በጭልፋ አስቀመጡ
ጭልፋዋ ስትሰበር
በዋንጫ ገለበጡ
አጃ ቆሎ ስንዴ ቆሎ
ይህችን ትተሽ ያችን ቶሎ

ምሳሌ፡- ገባች እና ልጆች

1. ________ እና ________
2. ________ እና ________
3. ________ እና ________
4. ________ እና ________
5. ________ እና ________

፫. የሚከተሉትን ሆሄያት በሳጥኑ ውስጥ ካሉ ቃላት ጋር በማዋሃድ ከፊደሉ ጎን ፃፉ::

1. ጨ፡- ______ ፣ ______
2. ጠ፡- ______ ፣ ______
3. መ፡- ______ ፣ ______

| | |
|---|---|
| ጨመረ | መሰንቆ |
| መረጠ | ጠበቀ |
| ጠፈር | ጨረቃ |

## መነጠልና ማጣመር

ë. የሚከተሉትን ቃላት ፊደላቱን በሚገባ በማንበብ በምሳሌው መሰረት ነጣጥላችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- የተለያዩ = የ-ተለያዩ

ከባህል = ከ-ባህል

1. ከእንጨት፡- ____________
2. የመሳሪያ፡- ____________
3. የሚሰራ፡- ____________
4. ከሽንበቆ፡- ____________
5. በከብት፡- ____________

ì. የሚከተለውን ፅሑፍ በማንበብ ፅሑፉን የሚወክለውን ፊደል ፃፉ፡፡

### እኔ ማን ነኝ…?

እስክስታ የምመታ ሰው እመስላለሁ፡፡ በ "ሸ" እና በ "በ"መካከል እገኛለሁ፡፡ በርካታ ቃላት ይመሰርቱብኛል፡፡ በፊደል ገበታ በዘጠነኛው መስመር ላይ እገኛለሁ፡፡ እኔ ማን ነኝ…?

📖 ንባብ



## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች ከትምህርታችሁ ጎን ለጎን ምን ምን ክበባት ላይ ትሳተፋላችሁ?
2. ክበባት ውስጥ ተሳትፎ የምታደርጉ ከሆነ ምን ምን ተግባራትን ታከናውናላችሁ?

## የባህል ቀን

ዕለቱ ሀሙስ ነው፡፡ ሜሮን ከትምህርት ቤት እንደገባች የደንብ ልብሷን ቀየረች፡፡ ወዲያውኑ ባህላዊ ዘፈኖችን ከፍታ መወዛወዝ ጀመረች፡፡ እናቷ ተደብቀው ያይዋታል፡፡ ልጃቸው የተለያዩ ውዝዋዜ መቻሏ ገርሟቸዋል፡፡ እናቷም ከልጅነት የዕድሜ ዘመናቸው ጀምሮ ባህላዊ ተወዛዋዥ በመሆን ያገለገሉ በመሆናቸው በትዝታ ተዋጡ፡፡ ድንገት ሜሮን "እማዬ" ብላ ተጣራች፡፡ እናቷም "አቤት ልጄ" አሏት፡፡ "ነገ በትምህርት ቤታችን የባህል ቀን ይከበራል፡፡ 'ሁላችሁም የተለያዩ ባህላዊ ልብሶች ልበሱ፡፡ ባህላዊ ጭፈራዎችንም ተለማመዱ፡፡' ተብለናል" አለቻቸው፡፡

## የሜሮን እናት በሜሮን ድርጊት የሚደሰቱ ይመስላችኋል?

እናቷም “ጥሩ ነው! ባህላዊ ሙዚቃዎቻችንና ባህላዊ ጭፈራዎቻችንን በሚገባ ማወቅ አለብን። እኛ ያወቅነውን ለእናንተ እናስተላልፋለን፡ እናንተ ያወቃችሁትን ደግሞ በመጨመር ለቀጣይ ትውልድ ታስተላልፋላችሁ። ይህ ሲሆን ባህላችን እንደተጠበቀ ይሆናል። ስለዚህ ቅድም ስትወዛወዢ እያየሁሽ ነበር። የተሳሳትሻቸው እንቅስቃሴዎች አሉ።” በማለት ማስተካከያ ሰጧት። ሜሮንም ትምህርት ቤት ሄዳ የባህል ቀን ላይ ጥሩ ውዝዋዜ አቀረበች። ባቀረበችውም ውዝዋዜ ተመልካቾች ስለተደሰቱ ብዙ ሽልማትን አገኘች ።

### አንብቦ መረዳት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን “እውነት” ስህተት ሆኑትን ደግሞ “ሐሰት” በማለት በቃል መልሱ።

1. የሜሮን እናት የባህላዊ ሙዚቃ ተወዛዋዥ ነበሩ።
2. በእነሜሮን ትምህርት ቤት የሚከበረው የሴቶች ቀን ነበር።
3. የሜሮን ችሎታ(ተሰጥኦ) ስነ ፅሑፍ ማዘጋጀት ነው።

### አቀላጥፎ ማንበብ

ተማሪዎች “የባህል ቀን” የሚለውን ምንባብ ተራ በተራ እየተነሳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።

## ቃላት

፩. ምንባቡን መሰረት በማድረግ በ "ሀ" ስር ያሉትን በ "ለ" ስር ካሉት ጋር እንደአገባባቸው አዛምዱ።

| ሀ | መልስ | ለ |
|---|---|---|
| 1. ውዝዋዜ | | ሀ. ተሳታፊ |
| 2. ጥሩ | | ለ. መልካም |
| 3. ተመልካች | | ሐ. እስክስታ |
| 4. ትዝታ | | መ. ልማድ |
| 5. ባህል | | ሠ. ትውስታ |

፪. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በተመሳሳይ ፊደል የሚጀምሩ ቃላትን መስርቱ።

ምሳሌ፡- /ዘ/ ሀ፡- ዘፈነ

ለ፡- ዘመረ

1. /ከ/ ሀ፡- ________
   ለ፡- ________
2. /በ/ ሀ፡- ________
   ለ፡- ________
3. /መ/ ሀ፡- ________
   ለ፡- ________

፫. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በተመሳሳይ ፊደል የሚጨርሱ ቃላትን መስርቱ።

ምሳሌ፡- ክራር እና ብድር

1. ሀ፡- ________
   ለ፡- ________
3. ሀ፡- ________
   ለ፡- ________

2. ሀ፡- ___________

ለ፡- ___________

፬. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን የሙዚቃ መሳሪያዎች ባህላዊና ዘመናዊ በማለት መድቧቸው።

ከበሮ ጊታር ፒያኖ በገና ማንዶሊን
ማሲንቆ ክራር ሳክስፎን ዋሽንት ኪቦርድ

| ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች | ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

## ጽሕፈት

፭. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ሁለት ዓረፍተ ነገሮች በሚገባ በማዳመጥ ደብተራችሁ ላይ ፃፉ።

፮. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በሚገባ በማንበብ በሳጥኑ ውስጥ የተቀመጡትን ስርዓተ ነጥቦች በመጠቀም አሟሉ።

| ? | ! |
|---|---|

1. ስንት ሰዓት ነው
2. የሜዳው ሳር በጣም ደስ ይላል
3. የባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያው ድምፅ ይማርካል
4. ባህል ማለት ምን ማለት ነው

፫. ተማሪዎች የሚከተሉትን ተግባራት በጋራ ሆናችሁ ስሩ፡፡

ሀ. በቡድን በቡድን ሆናችሁ ተቀመጡ፡፡

ለ. ባህላዊ ሙዚቃን በተመለከተ ሁላችሁም የየራሳችሁን ሶስት ሶስት ጥያቄዎች ፃፉና እርስ በርስ ተቀያየሩ፡፡

ሐ. ላወጣችኋቸው ጥያቄዎች በጋራ በመሆን በፅሁፍ ምላሽ ስጡ፡፡

መ. በጋራ በመሆን ላወጣችኋቸው ጥያቄዎች የተሰጠው መልስ ላይ ተነጋገሩ፡፡

## የማጠቃለያ ተግባር

፩. የሚከተሉትን ቃላት ፊደላቱን በሚገባ በማንበብ የመጀመሪያ ፊደላቸውን ከቃሉ በመነጠል ጻፉ፡፡

ሀ. የጭፈራ

ለ. ለሙዚቃ

ሐ. በሥርዓት

መ. ከሰርግ

ሠ. በእንቢልታ

ረ. የነጋሪት

፪. የሚከተለውን ተግባር በአጠያየቁ መሰረት መልሱ፡፡

እስኪ አወቁኝ...?

ከእንጨት የምሰራ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ነኝ፡፡ቁመቴ ረጅም ነው፡፡ በውስጤ አስር አውታሮች (ክሮች) አሉኝ፡፡ ለስለስ ያለ ድምፅ ስለማወጣ በርካታ ሰዎች ይወዱኛል፡፡ ብዙ ጊዜ ለመንፈሳዊ አገልግሎት እውላለሁ፡፡ በአንዳንድ መንፈሳዊ በዓላት ላይ የምገኝ እኔ ማን ነኝ...?



አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሰባት

## መልካም ስነ ምግባር

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ባዳመጣችሁት ፅሑፍ ውስጥ ያሉ አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም ነጠላ ዓ.ነገሮችን ትመሰርታላችሁ።
- ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ።
- ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ትዘረዝራላችሁ።
- በተገቢ ፍጥነት አጫጭር ታሪኮችን ታነባላችሁ።
- የተሰጣችሁን ቃላት በትክክል ትፅፋላችሁ።

## ማዳመጥ

### ትክክለኛ ዳኛ



### ቅድመ-ማዳመጥ

1. በምትማሩበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሲጣሉ ምን ታደርጋላችሁ?
2. ከላይ የቀረበውን ምስል በትኩረት በመመልከት የተረዳችሁትን ሐሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## አዳምጦ መናገር

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን "እውነት" ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ፡፡

1. ዳኛው ከፍትህ ይልቅ ለወዳጅነት ያደላል፡፡
2. ለጓደኛ ማዳላት የትክክለኛ ዳኛ መገለጫ ነው፡፡
3. አቶ አርፋሶ የፍርድ ቤት ዳኛ ናቸው፡፡
4. ዳኛው መልካም ስነ ምግባር ያለው ነው፡፡

፪. መምህራችሁ ያነበቡላችሁ ምንባብ ውስጥ ባሉ ቃላት አምስት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ሲራጅ የቅርብ ወዳጄ ነው፡፡

## ቃላት

፩. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ በ"ሀ" ስር የቀረቡትን ቃላት ከ"ለ"ስር ካሉት ቃላት ተቃራኒያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እውነተኛ | ሀ. ጠላት |
| 2. መጣ | ለ. ሐሰተኛ |
| 3. ወዳጅ | ሐ. ጥላቻ |
| 4. ፍቅር | መ. ሔደ |
| 5. ክብር | ሠ. ውርደት |


፪. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላት በትኩረት በማንበብ ተመሳሳይ የመድረሻ ፊደል ያላቸውን ቃላት በተሰጡት ምድቦች አስገቡ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በላች | የዋህነት | አየች | ጫማዎች | ተማሪዎች |
| ገበሬዎች | በጎነት | ቸርነት | ሰራች | |

| በ"ች" የሚጨርሱ | በ"ዎች" የሚጨርሱ | "በነት" የሚጨርሱ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |

## መነጠልና ማጠመር

በምሳሌው መሰረት በክቡ ውስጥ ያለውን ቃል ከሌሎቹ ቃላት ጋር አጣምሩ፡፡




ሀ. መልካም ሰው

ለ. መልካም ምግባር

ሐ. መልካም ስራ

መ.__________

ሠ.__________

ረ.__________

ሰ.__________

## 📖 ንባብ

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች ፊደል የት እንደተማራችሁ ታስታውሳላችሁ?

2. አዎ ካላችሁ ምን ምን ነገሮችን እንደምታስታውሱ ተናገሩ።

### "ሀሁ..."



አንድ ትንሽ ልጅ ወደአንድ ታላቅ የኔታ ዘንድ ሄዶ "ሀ ሁ" ይቆጥር ነበር። ወላጆቹም እጁን ይዘው መንገድ ያሻግሩትና ከየኔታ ጋር ያገናኙታል። የኔታም ወደክፍል ያስገቡትና ፊደል እንዲቆጥር ያደርጉታል። አንድ ቀን ይሄው ተማሪ እያለቀሰ ወደቤቱ መጣ። አባቱም "ምነው? ምን ሆነህ ነው የምታለቅሰው?" ሲሉ ይጠይቀዋል።

ልጅ፡- "የኔታ ተቆጡኝ!"

አባት፡- "መቼም ሳታጠፋ ዝም ብለው አይቆጡህም፤ በል እውነቱን ንገረኝ! ከዋሸህ እኔም እቀጣሃለሁ!" አለው፡፡

ልጅ፡- "መነሻውማ 'ሀ' በል ሲሉኝ ዝም ስላልኳቸው ነው!" አለ፡፡

አባት፡- ተናደደና "አንተ እንዴት ዝም ትላለህ? 'ሀ' ማለት አቅቶህ ነው?" ብሎ በንዴት ጠየቀው፡፡

ልጅ፡- "አይ አባዬ አላቃተኝም፤ ግን እሱን ብቻ አይጠይቁም፡፡"

አባት፡- "እና ምንድን ነው የሚጠይቁህ?"

ልጅ፡- 'ሀ' ስትል 'ሁ' በል ይሉሃል፡፡ 'ሁ' ብዬ ተገላገልኩ ስትል 'ሂ' በል ይሉሃል፡፡ እንዲህ እያሉ እስከ 'ፐ' ያስለፈልፉሃል! አያድርስብህ አባዬ!" አለና መለሰ፡፡

አባት በልጁ ስንፍና ደነገጠ፡፡

አባት፡- "ልጄ ያንተኮ ስራ መማር ነው፡፡ የኔታ ደጋግመው የሚያስተምሩህ ጥሩ እውቀት እንዲኖርህ ነው፤ ስለዚህ ከነገ ጀምሮ በርትተህ መማር አለብህ፡፡" ብሎ መከረው፡፡ልጁም የአባቱን ምክርና የመምህሩን ትምህርት ተቀብሎ ጎበዝ ተማሪ ሆነ፡፡

## አንብቦ መረዳት

፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ትንሹ ልጅ የኔታ ጋር እንዲሄድ የተደረገው ለምንድን ነው?

   ሀ. እንዲረብሽ    ለ. እንዲማር    ሐ. እንዲሰለች

2. ልጁ ከተመከረ በኋላ ምን ሆነ?

   ሀ. ሰነፍ ተማሪ    ለ. ስልቹ ተማሪ    ሐ. ጎበዝ ተማሪ

3. በምንባቡ ውስጥ "ተገላገልኩ" የሚለው ቃል አገባባዊ ፍች ምንድን ነው?

   ሀ. ጨረስኩ    ለ. ጀመርኩ    ሐ. ደከመኝ

፪.ተማሪዎች በቡድን ሆናችሁ "ሀሁ..."የሚለውን ምንባብ ዋና ሐሳቡን በአጭሩ ፃፉ።

## ቃላት

፩. ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት ፍቺ ስጡ።

1. መማር
2. ጥበቃ
3. መንገድ
4. እውቀት
5. ምክር

፪. በ"ሀ" ስር ያሉትን ምልክቶች ከ"ለ" ስር ካሉት ስያሜያዎቻቸው (መጠሪያዎቻቸው) ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. X | ሀ. ማካፈል |
| 2. ÷ | ለ. ማባዛት |
| 3. + | ሐ. መቀነስ |
| 4. - | መ. እኩል ይሆናል |
| 5. = | ሠ. መደመር |

ፎ. የሚከተሉትን ምልክቶች ከዓረፍተ ነገሮቹ ጋር በማጣጣም አገናኙ፡፡

| X አብዛ | + (ጨምር) | - (ቀንስ) | ÷ (አካፍል) | = (እኩል) |
|---|---|---|---|---|

1. መልካምነትህን X (አብዛ)
2. ያለህን ለሌለው ________
3. ደግነትና የዋህነትን ________
4. ስንፍናን ________
5. ለሁሉም________አመለካከት ይኑርሽ/ህ፡፡

## አቀላጥፎ ማንበብ

"ሀሁ..." የሚለውን ምንባብ በተገቢው የአነባበብ ስልት ደጋግማችሁ በማንበብ እንደአባትና ልጅ በመሆን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃላችሁ አቅርቡላቸው፡፡

## ✍ጽሕፈት

ፏ. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒያቸውን በመፈለግ ጻፉ፡፡

1. ደግ፡-________
2. ሰነፍ፡-________
3. ጥሩ፡-________
4. ውሸት፡-________
5. ምርቃት፡-________

፪. በተሰጣችሁ ሰንጠረዥ መልካም ምግባር እና መጥፎ ምግባር የሚባሉትን ተግባራት በየምድባቸው ፃፉ።

| መልካም ስነ ምግባር | መጥፎ ስነምግባር |
|---|---|
| ሠውን መርዳት | መስረቅ |
| 1. | 1. |
| 2. | 2. |
| 3. | 3. |

በሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሰረት ዓረፍተ ነገር ስሩ።

ምሳሌ፡- ጓደኛ፡- የብርቱካን ጓደኛ ታማኝ ናት።

ዳኛ፡- አቶ ሲራጅ ዳኛ ናቸው።

1. ፍርድ ቤት፡-______________________________
2. መከባበር፡- ______________________________
3. ትህትና፡-______________________________
4. መታዘዝ፡-______________________________
5. ደግነት፡-______________________________

## የማጠቃለያ ተግባር

፩. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላት በትኩረት በማንበብ ተመሳሳይ የመድረሻ ፊደል ያላቸውን ቃላት በተሰጡት ምድቦች አስቀምጡ።

መጣን አነበብን በላህ ገዛህ ተኛህ

መልካምነት ልጅነት በጎነት ሰጠን

| በ"ን" የሚጨርሱ | በ"ህ" የሚጨርሱ | በ"ነት" የሚጨርሱ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |

፪. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ።

1. መርዳት፡- ______________________
2. አረጋውያን፡- ______________________
3. ምግባር፡- ______________________
4. መተባበር፡- ______________________
5. ጥላቻ፡- ______________________

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ስምንት
## የምግብ አዘገጃጀት

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ካዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ዋናውን መልዕክት ታደራጃላችሁ።
- ካዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ትሰጣላችሁ።
- ከምንባብ ውስጥ ተራ ዓረፍተ ነገሮችን ትለያላችሁ።
- ተመሳሳይ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ትዘረዝራላችሁ።
- አጫጭር ታሪኮችን አቀላጥፋችሁ ታነባላችሁ።

## ማዳመጥ

### ተጋቢኖ



### ቅድመ-ማዳመጥ

3. ተማሪዎች በቤታችሁ ውስጥ ምን ምን ምግቦችን ታዘጋጃላችሁ?
4. በቤታችሁ ውስጥ ከሚዘጋጁ ምግቦች አንዱን መርጣችሁ አሰራሩን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

### አዳምጦ መናገር

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን "እውነት" ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ።

1. ብሩክ የሰራው ዶሮ ወጥ ነው።
2. ተጋቢኖ ለመስራት የግድ ዘይት ያስፈልጋል።
3. የብሩክ እናት የሄዱት ሰርግ ነው።

፪. የምንባቡን ታሪክ በቅደም ተከተል በማምጣት በዓ.ነገር አስቀምጡ፡

| | |
|---|---|
| መጀመሪያ | ብሩክ እናቱ ለቅሶ ስለሄዱ ወጥ አልቆበት ራበው። |
| ከዚያ | |
| በመቀጠል | |
| በመጨረሻ | ብሩክ ምሳውን ከእናቱ ጋር በላ። |

ቃላት

፩. ለሚከተሉት ቃላት ምንባቡን መሰረት በማድረግ ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።


| ቃላት | ተመሳሳይ ፍቺ |
|---|---|
| 1. ጠዋት | |
| 2. በልቶ | |
| 3. አይቼ | |
| 4. መጠነኛ | |
| 5. ከለሰ | |

፪. በሚከተሉት ቃላት ላይ ያሉትን መነሻ ሆሄያት በምሳሌው መሰረት ለይታችሁ አመልክቱ፡

ምሳሌ፡- ስለበላ = ስለ-በላ ወደቤት = ወደ-ቤት

1. እንደፃፈ፡- ______________
2. የተቀባ፡- ______________
3. ከሰራ፡- ______________
4. ስለጠጣ፡- ______________
5. ለእናት፡- ______________

፫. የሚከተሉትን ስዕሎች ከመጠሪያቸው (ስማቸው) ጋር አዛምዱ።

| ምስሎች | መልስ | መጠሪያ |
|---|---|---|
| 1  | | ሀ. ቆስጣ |
| 2  | | ለ. ድንች |
| 3  | | ሐ. ሙዝ |
| 4  | | መ. ፓፓዬ |
| 5  | | ሠ. በቆሎ |

# ንባብ



## ቅድመ ንባብ

1. የተመጣጠነ ምግብ ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

2. ከስዕሉ ምን ትገምታላቹሁ ?

## የተመጣጠነ ምግብ

ለሰው ልጆች ከሚያስፈልጓቸው መሰረታዊ ነገሮች አንዱ ምግብ ነው። ምግብ የሰው ልጆች ጤነኛና ጠንካራ እንዲሆኑ ያደርጋል። የሰው ልጆች ደግሞ ጤነኛና ጠንካራ የሚሆኑት የተመጣጠነ ምግብ ሲያገኙ ነው።

የተመጣጠነ ምግብ የምንላቸው ከእንስሳት ተዋፅኦ፣ ከተክሎች፣ከፍራፍሬ ውጤቶች፣ ከአዝዕርት ምርቶች... የሚገኙትን ነው።የሰው ልጆች ከእነዚህ ውጤቶች በየዕለቱ ማግኘት ከቻሉ ጠንካራና ጤነኛ ይሆናሉ።

ተማሪዎች ከእንስሳት ምን ምን ምግቦችን እናገኛለን ?

ከእንስሳት ተዋፅኦ የሚገኙት እንደቅቤ፣ ወተት፣ እንቁላል፣ ስጋ ወዘተ... ናቸው።ከአትክልቶች እንደ ቲማቲም፣ ድንች፣ ካሮት፣

ጎመን፣ ቆስጣ... ይገኛሉ። ከፍራፍሬ ውጤቶች ደግሞ ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ...ይመደባሉ። ከአዝእርት ምርቶች ስንዴ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ገብስ...ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ ግብኣቶች የምናገኘው ምግብ ለሰውነታችን ኃይልና ሙቀት ይሰጣል፤ በሽታም ይከላከላል፤ ሰውነታችንን ይገነባል። ስለዚህ እነዚህን ምግቦች በአግባቡና በንፅህና በማዘጋጀት መመገብ ያስፈልጋል።

## አንብቦ መረዳት

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል ሆኑትን "እውነት" ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ።

1. የተመጣጠነ ምግብ ለጤና አስፈላጊ ነው።
2. በምንባቡ ውስጥ አምስት አራት ነጥቦች ብቻ አሉ።
3. የሰው ልጆችን ጤነኛና ጠንካራ የሚያደርጋቸው ምግብ ነው።

## ቃላት

፩. የሚከተሉትን ቃላት በየመደባቸው አስቀምጡ።




ጎረሰች ረጅም ተጋቢኖ ወጥ በላ ቀጭን
ዳቦ እንጀራ ወፍራም ጠጣ ሰራች አጭር

| ድርጊት የሚያሳዩ | የምግብ መጠሪያ | መጠንን የሚገልፁ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

፪. በ"ሀ" ስር ያሉትን በ"ለ" ስር ከሚገኙት ተስማሚ ቃላት ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
| --- | --- |
| 1. ምጣድ | |
| 2. ማማሰያ | |
| 3. ጭልፋ | ሀ. ለእንጀራ |
| 4. ድስት | ለ. ለወጥ |
| 5. ሞሶብ | |
| 6. ሰፌድ | |

፫. በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን የድርጊቶች ምስሎች ከመጠሪያቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ምስሎች | መልስ | መጠሪያ |
| --- | --- | --- |
| 1  | | ሀ. መግመጥ |
| 2  | | ለ. መብላት |
| 3  | | ሐ. መጠጣት |
| 4  | | መ. መክተፍ |
| 5  | | ሠ. መቁረጥ |

## ✍ጽሕፈት

፩. የተመጣጠነ ምግብ ከሚለው ምንባብ ውስጥ ሶስት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

፪. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

1. መክተፊያ፡-__________________________________

2. ማንቆርቆሪያ፡-________________________________

3. ቢላዋ፡-______________________________________

፫. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ታሪክ መሰረት በማድረግ አንድ የምታስታውሱትን በዓል መርጣችሁ ታሪክ ፃፉ፡፡

- ስትፅፉ የሚከተሉትን ጉዳዮች አካቱ፡-
  - ሀ. የበዓሉ ስም፣ ቦታ እና ጊዜን
  - ለ. በበዓሉ ላይ ያጋጠማችሁ ገጠመኝ
  - ሐ. በዓሉ የተጠናቀቀበት ሁኔታ…

## የማጠቃለያ ተግባራት

፩. የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ ተስማሚ የሆኑ ቃላትን በመፈለግ አጣምሩ።

ምሳሌ፡- ልብስ፡- ልብስ ሰፊ

1. ፀጉር፡- ________________ቀለም፡- ______________
2. ዶሮ፡- _________________ዜና፡- ________________
3. መዝሙር፡- ____________

፪. በሰንጠረዡ ውስጥ የተለያዩ ፊደላት ቀርበዋል፤ ፊደሎችን ወደላይ፣ ወደታች፣ ወደጎን እንዲሁም አግድም በማገናኘት ቃላትን መስርቱ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መ | ጋ | ዝ | ቅ | ቤ |
| ጥ | ዘ | ን | ባ | ባ |
| ረ | ሃ | ብ | ት | ህ |
| ጊ | ታ | ር | ጉ | ል |
| ያ | ቤ | ተ | ሰ | ብ |

# ምዕራፍ ዘጠኝ
## ዲጅታል ቁስ

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ካዳመጣችሁት የምንባብ ጽሑፍ ውስጥ ዋናውን መልዕክት ታደራጃላችሁ፡፡
- ካዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ቃላትን ከቅጥያዎች ጋር ታነባላችሁ፡፡
- ዓረፍተ ነገር በትክክል ትጽፋላችሁ፡፡

## ማዳመጥ

### መረጃ ማግኛ ቁሶች




### ቅድመ-ማዳመጥ

1. መረጃ ማግኛ ቁሶች የሚባሉት እነማን ናቸው?
2. ከላይ የቀረበውን ምስል በትኩረት በመመልከት የተረዳችሁትን ሐሳብ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

### አዳምጦ መናገር

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

1. የድሮው የመረጃ ልውውጥ ከአሁኑ በምን ይለያል?
2. መረጃን በፍጥነትና በሁሉም ቦታ ለማድረስ የሚያገለግሉ ዲጂታል ቁሶችን ዘርዝሩ፡፡
3. በዲጅታል ቁሶች ህይወትን የምናቀለው እንዴት ነው?

፪. የመረጃ ማግኛ ቁሶችን ጥቅምና ጉዳት በተመለከተ በቡድን መስርታችሁ ተወያዩ። የተወያያችሁትን ሀሳብ በቡድን መሪያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

## ቃላት

፩. የሚከተሉትን ቃላት ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ፍቺ ስጡ።

1. ቁስ፡-________________
2. ማስተሳሰር፡-____________
3. ማዳረስ፡-______________
4. መረጃ፡-____________
5. ልውውጥ፡-________

| ምስሎች | መልስ | መጠሪያ |
|---|---|---|
| 1.  | | ሀ. ካሜራ |
| 2.  | | ለ. ቴሌቪዥን |
| 3.  | | ሐ. ላፕቶፕ |
| 4.  | | መ. ሞባይል |
| 5.  | | ሠ. ራዲዮ |

# 📖 ንባብ



## ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. እቤት ስትሆኑ ብዙ ጊዜያችሁን የምታሳልፉት ምን በመስራት ነው?

2 ምስሉን አይታችሁ የምታነቡት ምንባብ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

## የጊዜ ብክነት

ጊዜው በጣም መሽቷል፤ አባት የሆነ ድምጽ ሲሰማ ከእንቅልፉ ነቃ፤ ሰዓቱን ተመለከተ። ከምሽቱ አምስት ተኩል ሆኗል። የምን ድምጽ እንደቀሰቀሰው ለማወቅ ከመኝታ ቤቱ ወጣ። ዳፋርሳ ስልኩ ላይ አፍጥጦ “ጌም” ሲጫወት አገኘው። አባቱም የልጁን ድርጊት በግርምት ተመለከተው። መለስ ብሎ በሀሳቡ የዳፋርሳን ውሎ መመርመር ጀመረ።

ዳፋርሳ ከትምህርት ቤት እንደተመለሰ የቀረበለትን ምግብ እንደነገሩ ቀማምሶ ቴሌቪዥኑን ከፈተው። የአሻንጉሊት ፊልም ሲያይ የእራት ሰዓት ደረሰ። እራቱን ጥቂት በልቶ የአባቱን ስልክ ይዞ ወደክፍሉ ገባ። ከክፍሉ ከገባ ጀምሮ አባቱ እስከተነሳበት ጊዜ ድረስ “ጌም” እየተጫወተ ነበር። አባቱም ልጁን እንደተመለከተ በዚያ ምሽት ምንም ነገር መናገር ስላልፈለገ እንዲተኛ ነግሮት ወጣ።

---

አባቱ በልጁ ድርጊት የተደሰተ ወይስ የተከፋ ይመስላችኋል?

---

ለሊቱም ነጋ የዳፋርሳ አባት ቀድሞ ተነሳና ቁርስ ሰራ። እናትም በመነሳት ቤቱን ማስተካከል ጀመረች። ዳፋርሳ ግን አልተነሳም ነበር። አባትም ዳፋርሳ በመቀስቀስ ስለኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች አጠቃቀም መምከር ጀመረ። እናትም “ልጄ ሙሉ ትኩረትህን ስልክና ቴሌቪዥን ላይ በማድረግህ ምግብ ለመብላትም ጊዜ አጥተሀል።

በተጨማሪም የተማርከውን የምታነብበት፣የቤት ሥራም የምትሰራበት ጊዜ ያስፈልግሀል፡፡ ስልክም ሆነ ቴሌቪዥን በአግባቡና በተወሰነ ጊዜ ከተጠቀምንበት ጠቃሚ ሲሆን ከልክ በላይ ከተጠቀምንበት ግን ጎጂ ነው፡፡” በማለት የራሷን ምክር ጨመረች፡፡ ዳፉርሳ የእናቱንና የአባቱን ምክር ትኩረት ሰጥቶ ሲያዳምጥ ከቆየ በኋላ ጥፋቱን አምኖ የተሰጠውን ምክር ተቀበለ፡፡ የእለት ክንውኑን መርጎ ግብር (ፕሮግራም) አውጥቶ ማንበብ ጀመረ፡፡

## አንብቦ መረዳት

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በጽሑፍ መልስ ስጡ፡፡

1. በምንባቡ ውስጥ ያሉ ሰዎች ብዛት ስንት ነው? ማንነታቸውን ግለጹ፡፡
2. ዳፉርሳ አባትና እናት ልጁን የመከሩት መቼ ነው?
3. የእናትና አባቱን ምክር ከሰማ በኋላ ምን አደረገ?

፪. ካነበባችሁት ምንባብ የተረዳችሁት መልዕክት በቡድን ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ የቡድናችሁን ሀሳብ በጽሑፍ ግለፁ፡፡

## ቃላት

፩. በምንባቡ መሰረት በ"ሀ" ስር ላሉት ቃላት ከ"ለ" ስር ካሉት ተቃራኒ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ።

| "ሀ" | መልስ | "ለ" |
|---|---|---|
| 10. ነቃ | | ሀ. ጠዋት |
| 11. ምሽት | | ለ. ቀነሰ |
| 12. ጨመረ | | ሐ. ተኛ |
| 13. አፍጥጦ | | መ. ብዙ |
| 14. ጥቂት | | ሠ. ጨፍኖ |

፪. በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት ፍቺ ስጡ።

3. ቀማምሶ
4. ጎጂ
4. ተመለከተ
5. በአግባቡ
5. ቀድሞ

### መነጠልና ማጠመር

፩. የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት አጣምራችሁ ፃፉ።ከዚያም የተነጣጠለውንና የተጣመረውን ጥንድ ሆናችሁ በመቀባበል አንብቡ።

| | | |
|---|---|---|
| ስነ | ምሳሌ፡- ስነ-ስርዓት | ሙከራ |
| | | ውበት |
| | | ስርዓት |
| ልበ | ምሳሌ፡- ልበ-ደንዳና | ብርሃን |
| | | ክርስትያን |
| | | ምግባር |
| ቤተ | ምሳሌ፡- ቤተ-ሙከራ | መጻሕፍት |
| | | ደንዳና |
| | | ቢስ |

፪. ከዚህ በታች ተነጣጥለው የተጻፉትን ቃላት አጣምራችሁ በመጻፍ አንብቧቸው፡፡

1. የ-ዜና፡-____________
2. ለ-መዝናኛ፡-____________
3. እየ-ተናገረ፡-____________
4. እንደ-ሄደ፡-____________
5. ተ-ገነባ፡-____________
6. ከ-መገናኛ፡-____________

## አቀላጥፎ ማንበብ

፩. "የጊዜ ብክነት" የሚለውን ምንባብ በሚከተለው መንገድ አንብቡ፡፡

ሀ. ደቂቃ በመያዝ በፍጥነት ደጋግማችሁ አንብቡ፡፡
ለ. ምንባቡን እየተከፋፈላችሁ በመቀባበል አንብቡ፡፡
ሐ. ስታነቡ ለማንበብ የጨረሰባችሁን ጊዜና የተፈጠረውን ስህተት በመከታተያ ቅጽ መዝግቡ፡፡

፪. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ሥርዓተ ነጥቦችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በትክክል አንብቡ፡፡

ሀ. ኤች አይ ቪ ኤድስ በደም ንክኪ ይተላለፋል፡፡
ለ. የቤት ሥራ ሳትሰራ እንዳትመጣ!
ሐ. ህጻናት ትምህርት ቤት የሚገቡት በስንት ዓመታቸው ነው?

## ✍ጽሕፈት

፩. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተ ነገሮች በማዳመጥ በትክክል ደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

፪.ባለፈው በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ከተማራችሁት ትምህርት ውስጥ ሁለቱን ተግባር በአራት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮች ጻፉ፡፡

## የማጠቃለያ ተግባር

**የሚከተለውን ፅሑፍ በትኩረት ካነበባችሁ በኋላ በተመሳሳይ ፊደል የሚጀምሩ እና የሚጨርሱ ቃላትን ለይታችሁ አውጡ።**

እቴሜቴ ሎሚ ሽታ፣
ያ ሰውዬ ምን አለሽ ማታ፣
ምንም ምንም ምንም
አላለኝ፣
ትዳሩን ፈትቶ ልውሰድሽ
አለኝ፣

አይወስድሽም ትዳሩን ፈትቶ፣
ምሎልሻል ጋሻ ጦር ደፍቶ፣
ማላ ማላ የጎበዝ ማላ፣
ፉት ይላታል እንደ ጉሽ ጠላ።

| በተመሳሳይ ፊደል የጀመሩ ቃላት | | በተመሳሳይ ፊደል የጨረሱ ቃላት | |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ፡- እንደ እና እቴሜቴ | | ምሳሌ፡- ማላ እና ጠላ | |
| 1. | | 1. | |
| 2. | | 2. | |
| 3. | | 3. | |
| 4. | | 4. | |
| 5. | | 5. | |

አማርኛ

፪ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አስር
## የዱር እንስሳት

### የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ካዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ዋናውን መልዕክት በጽሑፍ ዘገባ ታቀርባላችሁ፡፡
- የምንባቡን ሐሳብ ከተጨባጭ ህይወታችሁ ጋር ታዛምዳላችሁ፡፡
- ቃልአጋኖን እና የጥያቄ ምልክትን ትጠቀማላችሁ፡፡
- አቀላጥፋችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ለደረጃው የሚመጥን ዓረፍተ ነገር ትፅፋላችሁ፡፡

## ማዳመጥ

### ብልጒ ዝንጀሮ



### ቅድመ ማዳመጥ

1. ተማሪዎች በምትኖሩበት አካባቢ እንስሳት ጉዳት ደርሶባቸው ብትመለከቱ ምን ታደርጋላችሁ?
2. ብልህ የሚለው ቃል ፍቺው ምንድን ነው?

### አዳምጦ መናገር

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ በቃል ምላሽ ስጡ፡፡

1. እነዘምዘም ትንሿን ዝንጀሮ ለመርዳት ያነሳሳቸው ማን ነው?
2. እናት ዝንጀሮ የወሰደችው ህፃን ስም ማን ይባላል?
3. እናት ዝንጀሮ ልጇን ባታገኝ የወሰደችውን የሰው ልጅ ምን የምታደርገው ይመስላችኋል?

፪. “ብልኋ ዝንጀሮ” በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን ምንባብ አጠቃላይ ሐሳብ በቃላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## ቃላት

፩. ለሚከተሉት ቃላት ምንባቡን መሰረት በማድረግ አገባባዊ(አውዳዊ) ፍቺ ስጡ።

| ቃላት | ዐውዳዊ ፍቺ |
|---|---|
| 1. ቅጠል | የረገፈ የዛፍ አካል |
| 2. የሰፈሩ | |
| 3. ወላጆች | |
| 4. መደናገጥ | |
| 5. ወጥታ | |
| 6. ወተት | |


፪. የሚከተሉትን ቃላት የመጀመሪያ ፊደል በማጥፋት በምትኩ ሌላ ፊደል በመጨመር ቃል መስርቱ።

ምሳሌ፡- ጠጣ ፡- <u>መ</u>ጣ

ነብር ፡- <u>ክ</u>ብር

1. ጅብ፡- __________
2. በሬ፡- __________
3. ቀበሮ፡- __________
4. ጉሬዛ፡- __________
5. ግመል፡- __________

፫. በ"ሀ" ስር ያሉትን የእንስሳት ምስሎች በ"ለ" ስር ካለው መጠሪያቸው ጋር አዛምዱ።

| ሀ ምስሎች | መልስ | ለ መጠሪያ |
|---|---|---|
|  1. | | 1. ቀጭኔ |
|  2. | | 2. ዝንጀሮ |
|  3. | | 3. የሜዳ አህያ |
|  4. | | 4. ዝሆን |
|  5. | | 5. አንበሳ |

## ንባብ



### ቅድመ ንባብ

1. ተማሪዎች ጦጣ የዱር ወይስ የቤት እንስሳ ናት?
2. ስለ ጦጣ የምታውቁትን እውነታ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ?

### ጦጣ

ጦጣ በመላው ኢትዮጵያ በበርካታ ቦታዎች ትገኛለች፡፡ የብልጠት ምሳሌ ሆናም በብዙ ተረቶች ውስጥ ትጠቀሳለች፡፡ ፊቷ ጥቁር ነው፡፡ ዙሪያውን በነጭ ፀጉር የተከበበ ነው፡፡ ፀጉሯ ከግራጫማ ጀምሮ እንደየስፍራው እስከ ቡናማ አረንጓዴ ነው፡፡ ወንዶቹ በአማካይ 5.5 ኪሎ ግራም ሲመዝኑ፤ ሴቶቹ ደግሞ 4 ኪሎ ገደማ ይመዝናሉ፡፡ ጅራታቸው ረጃጅም ነው፡፡

ርዝመታቸው ጅራታቸውን ሳይጨምር ከ45 እስከ 83 ሴንቲ ሜትር ይሆናል፤ ጅራታቸው ደግሞ ከ55 እከ 114 ሴንቲ ሜትር ይሆናል፡

## ተማሪዎች ጦጣዎች ምን ምን የሚመገቡ ይመስላችኋል?

የጦጣዎች አኗኗር በቡድን ነው፡፡ በአንድ ቡድን ያሉ ጦጣዎች በመልክ እና በድምፅ ይተዋወቃሉ፡፡ በተጨማሪም በድምፅና በሰውነታቸው አኳኋን መልዕክት ይለዋወጣሉ፡፡ በየጊዜው የሚለዋወጠው የጅራታቸው ቅርፅ የሚያስረዳው ጉዳይ አለው፡፡ ወደፊት ሲያመለክት በራሱ የመተማመን ምልክት ነው፤ጫፉ ወደ ኋላ ሲያመለክት ደግሞ የመፍራት ምልክቱ ነው፡፡

በድምፅ መልዕክት ይለዋወጣሉ፤ እነሱን ሊያጠቃ የመጣ ጠላት ካለ እንደ ጥላታቸው ዓይነት ድምፃቸውን በመቀየር ይግባባሉ፡፡ሁለት ጦጣዎች ሲገናኙ በወዳጅነት ከሆነ ማለትም ለማከክ፣ ለመጫወት፣ ለመላፋት ወዘተ አፍንጫ ለአፍንጫ ይነካካሉ፡፡

አብዛኛዎቹ ጦጣዎች የሚወልዱት በዓመት አንድ ጊዜ ነው፡፡ ልጆቻቸውንም እያጠቡና እየተንከባከቡ ያሳድጋሉ፡፡ጦጣዎች የተገኘውንና በብዛት ያለውን ምግብ ነው የሚበሉት ፍራፍሬ፣ ጥራጥሬ፣ ቅጠላቅጠል፣ ሳሮች፣ ትላትሎች፣ እንሽላሊቶች፣ እንቁላልና በጎጆ ውስጥ ያሉትን አዕዋፍን ይመገባሉ፡፡

ጦጣዎች ብዙ ጠላት አላቸው፤ ጭልፊት፣ የሎስ(አሞራ)፣ ነብር፣ አነር፣ ከጠላቶቻቸው ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

## አንብቦ መረዳት

፩ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆኑትን "እውነት" ስህተት የሆኑትን ደግሞ "ሐሰት" በማለት በፅሁፍ መልሱ፡፡

1. ጦጣዎች የቤት እንስሳት ናቸው፡፡
2. የጦጣ የጅራት ቅርፅ ወደኋላ ካመለከተ የጦጣውን በራስ የመተማመን ሁኔታ ያሳያል፡፡
3. ጦጣዎች አትክልት ብቻ ተመጋቢ እንስሳት ናቸው፡፡

## ቃላት

፩. በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በመጠቀም የተለያዩ የዱር እንስሳትን ስሞች ፃፉ፡፡

| የተዘበራረቁ ፊደላት | የተመሰረቱ ቃላት | |
|---|---|---|
| ድ ዝ ል ጣ ሮ ብ ን በ ሆ ጦ ዋ ር ላ ቀ ጅ ኩ ጀ ኤ ነ ዝ ያ ጭ | ጦጣ | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

፱.የሚከተሉትን ፊደላት በመጠቀም የተለያዩ ቃላትን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ጠ፡- ጠርሙስ፣ ጠረጴዛ፣ ጠነከረ…

1. ከ፡- ________ ፣ ________ ፣ ________
2. ቀ፡- ________ ፣ ________ ፣ ________
3. መ፡- ________ ፣ ________ ፣ ________
4. አ፡- ________ ፣ ________ ፣ ________
5. ደ፡- ________ ፣ ________ ፣ ________

## አቀላጥፎ ማንበብ

"ጠጣ" የሚለውን ምንባብ ተራ በተራ እየተነሳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ድምፅ በማሰማት አንብቡላቸው፡፡

## ✍ጽሕፈት

መምህራችሁ በሰሌዳ ላይ የፃፉላችሁትን ዓረፍተ ነገሮች ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን በማካተት ጻፉ፡፡

## የማጠቃለያ ተግባር

፩. ከዚህ በታች የቀረበውን ፅሑፍ አንብባችሁ ምላሻችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

**እኔ ማን ነኝ?**

በጣም ጠንካራ ነኝ፡፡ ጥንካሬዬን የማገኘው በተወለድኩ በሶስተኛው ቀን የአባቴን ድምፅ ስሰማ ነው፡፡ የእንስሳት ንጉስም እባላለው፡፡ ኩሩ እንስሳ ነኝ፡፡ በእርጅና ዘመኔ ጉልበቴ ይደክማል፡፡ በአመጋገብ ስርዓቴ ግን ጥንቁቅ ነኝ፡፡ የሞተ ነገርና ህፃናትን አልመገብም፡፡ ስተኛ ዓይኔን የማልጨፍን የዱር እንስሳ ነኝ፡፡ እኔ ማን ነኝ...?

፪. ተማሪዎች ከቤተሰቦቻችሁ፣ ከምታውቁት ሰው ጠይቃችሁ ወይም ከመፅሃፍት አንብባችሁ ስለአንድ የቤት እንስሳ ባህርይ ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

፫. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን የእንስሳ ስሞች የቤት እና የዱር በማለት ፃፉ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዶሮ | ቀጭኔ | ድመት | ላም | የሜዳ አህያ |
| ሰጎን | በሬ | ቀበሮ | ዝሆን | በግ |

# ዋቢ ጽሑፎች

ሰለሞን ይርጋ። (2000)። አጥቢዎቹ። አዲስ አበባ፣ Limited Printers።

በላይነሽ ወርቁ። (2011)። ብልኋ ዝንጀሮ። አዲስ አበባ፣ USAID-RED II Project

በላይነሽ የሻው እና ቢረሳው ታደሰ። (2010)። Comet Supplementary Books Series: አማርኛ 3ኛ እና 4ኛ። አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት።

በጽሐ ዓለሙ (መ/ር)። (2011)። ምዕላደ ጥበብ። ደብረ ታቦር፣ ከኑ ማተሚያ ቤት።

ባህሩ ዘርጋው። (2010)። ዘርጋው መለስተኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ ርኆቦት አታሚዎች።

አላምረው ገ/ማርያም። (2002)። የአማርኛ መማሪያ አጋዥ መጽሐፍ (ከ1ኛ-4ኛ ክፍሎች)። አዲስ አበባ፣ አልታ ማተሚያ ቤት።

አዲስ አድማስ ጋዜጣ። (2011)። ግንቦት፣2011።

ከበደ ሚካኤል። (1999)። ታሪክና ምሳሌ። ኢትዮጵያ፣ ሜጋ አታሚ ድርጅት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)። (1993)። አማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

GPS My City. (2021). Hamle 19 Public park. Retrieved July 28, 2021. From፡ https://www.gpsmycity.com/attractions/hamle-19-public-park-44452.html

# የቃላት ፍቺ

| | |
|---|---|
| ሌጦ | ለሽያጭ የተዘጋጀ የበግ ወይም የፍየል ቆዳ |
| መቃ | ለመፃፊያነት የሚውል ቀለም መንከሪያ |
| መባቻ | መጀመሪያ ( ለሳምንት፣ ለወርና ለዓመት) |
| መግራት | ማስተካከል፣ ማሰልጠን |
| ሙዜም | የተለያዩ ቅርሶች ማስቀመጫ ማዕድ |
| ማግስት | ቀጣይ ቀን |
| ሞክሼ | አንድ አይነት መጠሪያ ያለው |
| ሰናይ | መልካም፣ ውብ፣ ደግ |
| ቁስ | መስሪያ ነገር፣ ቦታ የሚይዝ |
| ቅርስ | በቅድመ ዘመን ታሪክና የተካበተ ሀብት |
| ባልንጀራ | ወዳጅ፣ ጓደኛ፣ ባልደረባ |
| ብልሃት | ጥበብ፣ ዘዴ፣ ዕውቀት |
| ብራና | ከበግና (ከፍየል) ቆዳ የሚሰራ ወረቀት የሚመስ መፃፊያ |
| ብርቅዬ | ልዩ፣ በአንድ ሀገር (ቦታ) ብቻ የሚገኝ |
| ብዕር | ከመቃ፣ ከላባ የተዘጋጀ መፃፊያ |
| ተሰጥኦ | ልዩ ዕውቀት፣ ችሎታ |
| ትስስር | ውህደት፣ ተባብሮ መስራት |
| አውታር | የበገና፣ የክራር ጅማት |
| እርጅና | ሽማግሌነትና አሮጊትነት፣ በእድሜ መግፋት |
| እኩይ | መጥፎ፣ ምግባረ ቢስ |
| እጀ ጠባብ | እጅጌው ጠባብና ረጅም የሆነ ልብስ |

| | |
|---|---|
| ከተራ | የጥምቀት ዋዜማ |
| ዋዜማ | ከዋና በዓል አስቀድሞ የሚውል ቀን |
| ውሽንፍር | ነፋስ የቀላቀለ ዝናብ |
| የኔታ | አስተማሪዬ፣ መምህሬ |
| ጀለቢያ | የእስልምና እምነት ተከታዮች የሚለበስ ረጅም ቀሚስ መሰል ልብስ |
| ጠንቅ | ሰበብ፣ መነሻ፣ መዘዝ |
| ጥልፍ | በተለያዩ ጨርቆችና ልብሶች ላይ በክርና መርፌ ተወሳስቦ የሚሰራ ጌጥ |
| ጥሞና | በዝምታ፣ በጥልቀት |
| ጥጃ | እንቦሳ፣ ያላደገ የእንስሳ (የላም) ልጅ |
| ጭጋግ | ጉም፣ ጢስ የሚመስል |

# የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሳልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

# የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| ከ1 እስከ 10 | | ከ11 እስከ 20 | |
|---|---|---|---|
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች | የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፩ | 1 | ፲፩ | 11 |
| ፪ | 2 | ፲፪ | 12 |
| ፫ | 3 | ፲፫ | 13 |
| ፬ | 4 | ፲፬ | 14 |
| ፭ | 5 | ፲፭ | 15 |
| ፮ | 6 | ፲፮ | 16 |
| ፯ | 7 | ፲፯ | 17 |
| ፰ | 8 | ፲፰ | 18 |
| ፱ | 9 | ፲፱ | 19 |
| ፲ | 10 | ፳ | 20 |
| **ከ20 እስከ 100** | | **ከ200 እስከ 1000** | |
| **የኢትዮጵያ ቁጥሮች** | **የአረብኛ ቁጥሮች** | **የኢትዮጵያ ቁጥሮች** | **የአረብኛ ቁጥሮች** |
| ፳ | 20 | ፪፻ | 200 |
| ፴ | 30 | ፫፻ | 300 |
| ፵ | 40 | ፬፻ | 400 |
| ፶ | 50 | ፭፻ | 500 |
| ፷ | 60 | ፮፻ | 600 |
| ፸ | 70 | ፯፻ | 700 |
| ፹ | 80 | ፰፻ | 800 |
| ፺ | 90 | ፱፻ | 900 |
| ፻ | 100 | ፲፻ | 1000 |

| ከ2000 እስከ 10000 | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች | የአረብኛ ቁጥሮች |
| ፳፻ | 2000 |
| ፴፻ | 3000 |
| ፵፻ | 4000 |
| ፶፻ | 5000 |
| ፷፻ | 6000 |
| ፸፻ | 7000 |
| ፹፻ | 8000 |
| ፺፻ | 9000 |
| ፻፻ | 10000 |